# ያገቡ ሴቶች ዜግነት በኢትዮጵያ ሕግ

ጌታቸው አበራ*

- ሀ -

በ1930 በወጣው የኢዮጵያ የዜግነት ሕግ ላይ ስለ አገቡ ሴቶች ዜግነት የሚያወሱት አንቀጾች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለተለያዩ ትርጓሜዎች መንስኤ ሆነዋል። በወ/ሮ ስሺትላና ማማዶቫና በአሜሪካን ኮሙኒቲ ት/ቤት መሐከል የተነሳው የሥራ ክርክር[1] ላይ ዋና አርእስት የሆነው ስለ አንዲት ከኢትዮጵያዊ ጋር ስለተጋባች ሩሲያዊት ዜግነት ጉዳይ ነበር፤ የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የማልማል ላኛ ወ/ሮ ስሺትላና ኢትዮጵያዊ ዜጋ ስላገባች፣ በዚሁ ጋብቻ ምክንያት ኢትዮጵያዊት ሆናለች ብሎ ወስንዋል። በይግባኝ ጉዳዩን የሰማው የአውራጃ ፍርድ ቤት ግን ወ/ሮ ስሺትላና ኢትዮጵያዊ ስላገባች ብቻ የኢትዮጵያ ዜጋ ልትሆን አትችልም ብሎ ወስንዋል። ይህም ውሳኔ በተጣይነት በአታቢ ሕግ ጽ/ቤት ተቀባይነት አግኝቷል።

የአውራጃው ፍ/ቤት ውሳኔ፣ ኢትዮጵያዊ ስላገቡ የውጭ ዜጋ ሴቶች ዜግነት ጉዳይ ሁለት ጠቃሚና አስፈላጊ ጥብጦችን ያነሳል፤ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት በውጭ አገር ዜጋ ሴቶችና በኢትየጵያ ዜጋ ወንዶች መሐከል የሚደረገው ጋብቻ በሴቶች ዜግነት ላይ ምን ውጤት ያመጣል? አንድ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤት፣ አንዲት ከኢትዮጵያዊ ጋር የተጋባች የውጭ ዜጋን፣ ሀተ ጣምራ ዜግነትን ይከለክላል በሚል ምክንያት ብቻ የኢትዮጵያ ዜግነት ሊከለክላት ይችላልን?

በዚህ ፅሁፍ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ያገቡ የውጭ አገር ሴቶችን ዜግነት በተመለከተ በ1930** በወጣው የኢትዮጵያ የዜግነት ህግ ውስጥ የተደነገጉት አንቀጾች፣ ከድር

---

* የትርፍ ጊዜ ሌክቸረር፣ ሕግ ፋኩልቲ፣ አዲስ አበባ ዮኒቨርሲቲ።

** በዚህ ፅሁፍ ውስጥ ያለው የጊዜ አቆጣጠር ሁሉ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ነው።

ጀምር በተለምዶ በሚታወቀው የቤተሰብ አንድነት መርህ ላይ የተመሠረቱ መሆናቸውን ለማሳየት ተሞክሯል። ለዚህም አላማ ሲባል ስላገቡ ሴቶች የሚያወሳውን የኢትዮጵያን የዜግነት ሕግ ትክክለኛ ትርጉሙን ለማስቀመጥ ስላገቡ ሴቶች ዜግነት የሚደነግገው ሕግ ዕድገት ተመርምሯል። በመቀጠልም ስለጣምራ ዜግነት አጠር ያለ ማብራሪያ ተሰጥቷል። ይህም የሆነው በዚሁ ጉዳይ ላይ የተለያዩ አስተያየቶችና ትርጓሜዎች ስለታዩ ነው። በ1930 ዓ.ም. የወጣው የዜግነት ሕግ ምንጮች ይሆናሉ የተባሉትን ሁኔታዎች ከገመገምን በኋላ ይህንን ሕግ በመጠቀም የአውራጃው ፍ/ቤት ኢትዮጵያዊ ስላገባች የውጭ አገር ሴት ዜግነት ጉዳይ የሰጠውን ብይንም እንመረምራለን። በመጨረሻም በማጠቃለያ መልክ በሕግ ማውጣትና በዳኝነት ሥራ መሐከል ያለውን ልዩነት፥ እንዲሁም አንዱ በሌላው ሥራ ጣልቃ ሲገባ በዝምታ ማለፉ የሚፈጥረውን ችግርና ውጤቶቹን በተመለከተ አንዳንድ አስተያየቶች ይሰጣሉ።

- ለ -

የዜግነት ፅንሰ ሃሳብ ዕድገት በቅድመ ሁኔታነት የሉዓላዊ አገሮችን መፈጠርና የአለም አቀፍ ግንኙነት መኖርን ይጠይቃል።[2] አንድ አገር ከሌሎች አገሮች ጋር አለም አቀፍ ግንኙነት ከሌለው ለዚያ አገር ህዝብ የዜግነት ህጎች መታወጅ ምንም ፋይዳ የለውም። ሌሎች አገሮች ከሌሉ እናም አለም አቀፍ ግንኙነት ከሌለ፥ ፓንሁይስ "አጋጣሚ ጉዳዮች"[3] ያላቸው ችግሮች አይነሱም። ብዙ አገሮች ባሉበት ሁኔታ ውስጥ የተጠናከረ የእርስ በርስ አለም አቀፍ ግንኙነት ስለሚኖር፥ በዚያን ወቅት አንድ ግለሰብ የዚህ ወይም የዚያ አገር ዜጋ ነው የሚል ችግር ይነሳ ይሆናል። አንድ ሰው የዚህ ወይም የዚያ አገር ዜጋ ነው ብሎ የመለየት ችግር በተጨባጭ መልኩ የተከሰተው የብሄራዊ ውትድርና አገልግሎት ግዴታ ሲጀመርና የብሄራዊ ፖለቲካዊ መብቶች ለዜጎች ሲታወጁ ነው።[4]

አንድ ግለሰብ የአንድ አገር ዜጋ ነው ብሎና ከሌሎች አገሮች ዜግነት ለይቶ መወሰን፥ በግዴታ በአገሮች መሐከል ግንኙነት መኖሩን ያሳያል። እንግዲህ ይህ የሚያሳየን የዜግነት ጥያቄዎች በመርህ ደረጃ መወሰን ያለባቸው በአለም አቀፍ ሕግ መሆኑን ነው።

ይሁን እንጂ፣ የዜግነት ፅንሰ ሐሳብ የቅርብ ጊዜ ክስተት በመሆኑ፣ እስም አቀፍ ሕግ እስካሁን ድረስ የዜግነትን ጉዳይ የሚዳኙ ተጨባጭ ሕጎች አላወጣም። እስም አቀፍ ህግ በደፈናው እያንዳንዱ አገር እነማን ዜጎቹ ሊሆኑ እንደሚችሉ በራሱ የውስጥ ሕግ የመወሰን መብት እንዳለው ይቀበላል።[5]

ስለዚህም ያገቡ ሴቶች ዜግነት በእያንዳንዱ አገር ሕግ መሠረት ይወሰናል ማለት ነው። ስለአገቡ ሴቶች ዜግነት ጉዳይ የሚደነግጉ የተለያዩ አገሮች የዜግነት ሕግ ድንጋጌዎች ከሁለት መሠረታዊ መርሆዎች በአንዱ ይመራሉ። አንደኛው መርህ ሚስት የባሏን ዜግነት እንድትይዝ ሲጠይቅ፣ ሁለተኛው መርህ ደግሞ ሚስት ዜግነቷን እራሷ እንድትመርጥ መብቷን ለእራስዋ ይተዋዋል። እስከ አንደኛው የእስም ጦርነት ማብቂያ ድረስ ብዙ አገሮች ያለ ልዩነት የመጀመሪያውን መርህ ይከተሉ ነበር፤ በዚህም መሠረት ጋብቻው ለሴትዮዋ የባሏን ዜግነት ይሰጣት ነበር። ሚስት የባሏን ዜግነት ማግኘትዋ ትክክል ነው በማለትም ብዙ ክርክሮች ቀርበዋል። አንደኛው ክርክር የቤተሰብን አንድነት ለመጠበቅ ሲባል ሚስት፣ ባልና እካለመጠን ያላደረሱ ልጆች ሁሉ አንድ ዓይነት ዜግነት ሊኖራቸው ይገባል የሚል ነው። የዚህ ክርክር መንፈስ ይህን ዓይነቱ ሥርዓት በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ባልና ሚስት ታማኝነታቸውን ለተለያዩና ምናልባትም ሊቃረኑ ለሚችሉ መንግሥታት ሲገልፁ የሚደርሰውን ችግር ያስቀራል የሚል ነው።

ባልና ሚስት ለተለያዩ የህግ ሥርዓቶች ተገዢ በሚሆኑበት ጊዜ በዜግነታቸው የሚጠበቅባቸውን ልዩ ልዩ ሕጋዊ ግዴታዎች ለመወጣት ሲሉ ከግልም ሆነ ከጋራ ህብታቸው ላይ በሚከፍሉበት ጊዜ በቤተሰቡ ላይ ከባድ ችግሮች ሲደርሱ ይችላሉ።[6] ከመንግሥት ተቅም አኳያ ሲታይም አንድ መንግሥት ሉዓላዊነቱን የሚቀበል፣ አንድ ወጥና ያልተከፋፈለ ቤተሰብ ይፈልጋል የሚል ክርክርም አለ። ብዙውን ጊዜ እንደሚታየው ሚስት ከጋብቻ በኋላ ወደ ባሏ የዜግነት አገር ትሄዳለች። እንዲሁም ማንኛውም በአንድ አገር ግዛት ውስጥ ያለ ሰው ለዚያ አገር መንግሥት ታዛዥነት ይጠበቅበታል። በተጨማሪም ከዚሁ ጋር ተያይዞ፣ ቤተሰብን እንደ አንድ የዜግነት መሠረታዊ አካል መውሰድ ለመንግሥት ያመቸዋል የሚል አስተያየትም አለ።

እዚሁ ላይ አንድ ግልፅ የሆነ ነገር አለ፤ ይኸውም የቤተሰብ አንድነትን ወይም አንድ ወጥ ለመንግሥት ታማኝነትን ለመጠበቅ ሲባል የአንዲት ሴት ፈቃድ ሳይጠየቅ የባሏን ዜግነት እንድትይዝ ማድረግ ሚዛናዊነት የጎደለው አሠራር ነው። ምክንያቱም ይህ ዓይነቱ አሠራር ሴትየዋን በቀጥታ በሚያገባት ጉዳይ እንደግለሰብነቷ ያላትን የማይገሰስ መብት አላወቀላትም።

ሚስት የባሏን ዜግነት እንድትይዝ በተደረገበት መንገድና፣ ባልየው የሚስቲቱን ዜግነት እንዲይዝ በማድረግ የቤተሰቡን አንድነትና አንድ ወጥ ለመንግሥት ታማኝነት ሊጠበቅ ይቻል ነበር። አብዛኛውን ጊዜ እንደታየው ሚስት የባሏን ዜግነት እንድትይዝ ይደረጋል እንጂ፣ ባል የሚስቱን ዜግነት እንዲይዝ አይደረግም።[7] አንዳንዴ ባል በሚስት የዜግነት አገር በሚኖርበት ጊዜ ዜግነትን ለማግኘት በሚደረገው ሥነ ሥርዓት ውስጥ የግል ተግባርና ፍላጎት አብረው እንዲገኙ ዕድል ይሰጣል። ይህንን ዕድል ግን ሚስት አታገኝም።

ይህ በአገሩ ሴቶች የዜግነት ህግ ላይ የሚታየው የሴቶችን መብት ከቁብ አለመቁጠር የኋላ ቀርነት ምልክት ነው። በፊውዳል ሥርዓት ማህበር ውስጥ ካቆጠቆጠው የወንድ ትምክህተኝነት በፊት የነበረው የአገሩ ሴቶች የዜግነት ህግ የተሻለ ሰብአዊነትና እኩልነት የሚታይበት ነበር። በጊዜው የነበረው ህግ በሮማውያን ህግ ውስጥ በታወቀው "ማንም ሰው ዜግነቱን እንዲቀይር ወይም በያዘው ዜግነት እንዲፀና አይገደድም" በሚለው መርህ ላይ የተመሠረተ ነበር።[8]

በአሜሪካን አገር እስከ 1855 ድረስ የዜግነት ማግኘት፣ ማቆየትና ማጣት ጉዳዮች የሚወሰኑት ዜግነቱ በሚመለከተው ሰው ፈቃድ ነበር። በእርግጥም ይህ ነፃነት ተፈጥሮአዊ እና የማይገሰስ የሁሉም ሰዎች መብት እንደሆነ የሚቆጠርና "በሕይወት፣ በነፃነት እና በደስታ ለመኖር" እጅግ አስፈላጊ መብት ተደርጎ ይታይ ነበር።[9]

ይሁን እንጂ ማንም ሊረዳው በሚችል መንገድ፣ ይህ የአሜሪካን ህግ አቋም ብዙም ሳይቆይ ወደ ወንድ ትምክህተኝነት ወጥመድ ገባ። በ1955 ዓ.ም. የአሜሪካን

ህግ አውጪ ምክር ቤት የአሜሪካ ዜግነትን አሜሪካዊ ባል ላገቡ የውጭ አገር ሴቶች የሚሰጥ ህግ አሳለፈ።[10] እንዲሁም በ1907 ዓ.ም. ይኸው ምክር ቤት ባወጣው ሌላ ህግ፥ አንዲት አሜሪካዊት ሴት የውጭ አገር ዜጋ ካገባች የባሏን ዜግነት እንደምትይዝ ወሰነ፥ ማለትም የአሜሪካ ዜግነቷን አጣች ማለት ነው።[11]

በዚህም እርምጃ የአሜሪካን የዜግነት ህግ "ዘመናዊ" ተደርጎ በብሪታኒያ የህግ ሥርዓት ከ1944 ጀምሮ ይሠራበት ከነበረው ከኮመን ሎው መርህ ጋር ሊጣጣም ችሏል። በእንግሊዝ አገር እስከ 1844 ድረስ የእንጊት ሴት ዜግነት በጋብቻ ምክንያት አይቀየርም የሚለው የኮመን ሎው መርህ ይሠራበት ነበር።[12] ይህ ህግ የብሪታኒያ ዜጋ ላገቡ የውጭ አገር ሴቶችም ሆነ የውጭ አገር ዜጋ ላገቡ የብሪታኒያ ዜጋ ሴቶች ይሠራ ነበር።[13] የዚህ ህግ መሠረት የሆነው ሀሳብ፥ አንድ ዜጋ ለሀገሩ ንጉሥ ያለው ታማኝነት በዚያ ሰው የግል ፈቃድ ሊቀየር አይችልም ከሚል ፊውዳላዊ የታማኝነት ፅንሰ ሀሳብ የመነጨ ነው።

ይህ የኮመን ሎው ህግ ግን በ1804 በወጣውና በጊዜው ዘመናዊ በነበረው በኮድ ናፖሊዮን የፈውዳል ህግ መቀየሩ አልቀረም። የኮድ ናፖሊዮን ህግ አንቀፅ 12 በፊት የነበረውን ህግ፥ ማለትም ፈረንሳዊ ያገባች የውጭ አገር ሴት የባሏን ዜግነት ማግኘቷን ሳይቀይር፥ በአንቀፅ 19 ላይ የውጭ ዜጋ ያገባች ፈረንሳዊት የባሏን ዜግነት እንደምታገኝ ደንግጓል። ይህ ድንጋጌ ከፊውዳሉ ህግ መርህ ጋር ሲወዳደር አንድ እርምጃ ወደፊት የተራመደ ነበር፤ ምክንያቱም በኮመን ሎው ህግ መሠረት አንዲት የውጭ ዜጋ ያገባች ሴት ለአገርዋ መንግሥት ያላትን ታማኝነት፥ የባሏን ዜግነት በማግኘቷ መቀየር አትችልም ነበር፤[14]

ይህ እንግዲህ በፈረንሳይ አብዮት መንፈስ ለሴቶች በከፊል ነፃነትን ያጎናፀፈ ነበር። ኮድ ናፖሊዮን በአውሮፓ አህጉር የዜግነት ህጎች ዕድገት ላይ ከፍተኛ ለውጥ ያስገኘ ነበር። ለምሳሌም በ1844 የብሪታንያ ፓርላማ አንድ ህግ አወጣ፤ በዚህም ህግ መሠረት አንዲት የብሪታኒያ ዜጋ ያገባች የውጭ አገር ሴት የብሪታንያን ዜግነት እንድታገኝ ፈቀደ። ይህ ከኮመን ሎው መርሆዎች ያፈተተ የመጀመሪያ እርምጃ ነበር። የብሪታኒያ የዜግነት ህግ በበለጠ ምሉዕ የሆነው በ1870 ፓርላማው ሌላ ህግ

ሲያወጣ ነበር፤ ይህም ህግ ማንኛቸም ያገባች ሴት ከባሏ ጋር በተጋቡበት ወቅት፣ ባሏ የያዘውን ዜግነት እንደያዘች እንድትቆጠር ደነገገ።[15]

እንደገናም በ1889 ዓ.ም. የፈረንሳይ ህግ ያገቡ ሴቶችን ዜግነት በተመለከተ ሌላ አዲስ መርህ አመነጨ፤ ይኸውም የኮድ ናፖሊዮንን አንቀፅ 12 በመቀየርና ተጨማሪ አንቀፅ በማያያዝ፣ የፈረንሳይ ሴት ጋብቻው የባሏን ዜግነት ካልሰጣት በስተቀር በጋብቻ ምክንያት ዜግነቷን እንደማታጣ ደነገገ።[16]

በኮድ ናፖሊዮን ላይ ያገቡ ሴቶችን ዜግነት በተመለከተ የተደነገጉት መርሆዎች ቀስ በቀስ በተለምዶ "የሰለጠነው አለም" በሚባሉት አገሮች ላይ ለውጥ አስከተሉ።

የዚህ ህግ ተፅእኖ በተለይም ከአንደኛው የአለም ጦርነት ማብቂያ በኋላ በእጅጉ አደገ። ወደ 1930 ዓ.ም. ገደማ 15 የሚሆኑ የአውሮፓ አገሮች የዜግነት ህጎች የውጭ አገር ሴት የባሏን ዜግነት የምታገኝበትን ህጋጋት ደነገጉ። አንዳንዶቹ የላቲን አሜሪካ አገሮችና አምስቱም የስካንዲኔቪያ አገሮች ተመሳሳይ ህጎችን አወጡ።[17]

- ሐ -

ከላይ እንደተገለፀው ዜግነት የተግባርና የፍላጎት ውጤት ነው፤ በመሆኑም አንድ ሰው በአንድ አገር ውስጥ እየኖረ የሌላ አገር ዜጋ ሊሆን ይችላል።[18] ይህ የሚያመለክተው፣ አንድ ሰው በተግባር እና በፍላጎቱ ካልሆነ በስተቀር ዜግነት ሊያገኝ ወይም ሊያጣ እንደማይችል ነው። ይህ አባባል ትክክል የሚሆነው ዜግነት የማግኘትም ሆነ የማጣት ጉዳዮች ከተገቢው ዜግነት የማግኛ ወይም ዜግነት የማጫ ህጋዊ ሥነ ሥርዓቶች ሲያያዙ ነው። ባገቡ ሴቶች ዜግነት ማግኘት ወይም ማጣት ጉዳይ ላይ ግን ይህ አባባል ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ወዲህና ከ20ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ በፊት እንደ ትክክለኛ አባባል አይታይም ነበር። እስከ አሁንም ድረስ ቢሆን ኢትዮጵያን ጨምሮ በብዙ አገሮች የህግ ሥርዓት ውስጥ እንደ ትክክለኛ አባባል አይቆጠርም።

በሌሎች አገሮች የዜግነት ሕጎች ዕድገት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያሳደሩት የኮድ ናፖሊዮን አንቀፅ 12 እና 19፣ የ1844ቱና የ1870ው የብሪታንያ ፓርላማ ህጎች፣ በ1855 እና በ1907 በአሜሪካን ኮንግሬስ የወጡት ህጎች፣ ሁሉ የተመሠረቱት ለመንግሥት ታማኝነትን በሚጠይቀው የፊውዳላዊ ጽንስ ሃሳብ ላይ ነው። በዚህም ምክንያት ለመንግሥት ያልተከፋፈለ የቤተሰብ ታማኝነትን ለማስገኘት ተብሎ፣ የቤተሰብ አንድነትን ለማምጣት በሚል ሽፋን፣ ከአገባቸው ሴት ነፃነት ይበልጥ የመንግሥት ጥቅም ቅድሚያ ተሰጥቶት ይታያል። ስለዚህም ጋብቻ በመፈፀሟ ምክንያት ብቻ ሚስት የባሏን አገር ዜግነት እንደያዘች ይቆጠር ነበር። የሴትዮዋ ፈቃደኝነት ዓይን ባወጣ መንገድ ተንቋል፤ አንዳንዴም እሷን በቀጥታ በሚመለከት ጉዳይ ላይ ፈቃደኛ ነች ተብሎ ሲገመት ቆይቷል።

ከ1922 በፊት በአሜሪካን አገር አሜሪካዊ ያገባች የውጭ አገር ሴት ፈቃደኝነቷ ሳይጠየቅ አሜሪካዊት ትሆን ነበር። በ1922 ጋብቻን አስመልክቶ በአንዲት አሜሪካዊ ባገባች ሴትና በባሏ መካከል በተደረገ ሙግት /በብሬደርና በዙብሪክ መካከል/፣ የአሜሪካ ፍ/ቤት የውጭ አገርዋ ሴት በዚያ ጋብቻ[19] ምክንያት የአሜሪካ ዜግነት አግኝታለች ብሎ ፈርዷል /አፅንኦት የተጨመረ/። ከ1922 በፊት በኬሊና በእወን ጉዳይ ተግባራዊ የሆነው ደንብ ሲሠራበት የቆየ ሲሆን፣ ይኸውም ከአንድ አሜሪካዊ ዜጋ ጋር የነበረ የጋብቻ ሁኔታ ዜግነትን ለማገኘት በቂ ነው የሚል ነበር።[20] በአጠቃላይ ሌላ ተቃዋሚ ህግ እስካልነበር ድረስ በጋብቻቸው ዘመን ሁሉ የሚስት ዜግነት የባሏ ዜግነት ነበር።[21]

አንዳንድ ጊዜም ሴትዮዋ ዜግነቷን የመተው ፈቃደኝነቷ ጋብቻውን በመፈፀሟ ይገመታል ተብሎ ተወስንዋል። በማኬንዚ እና በሄር መካከል በተደረገ ክርክር የአሜሪካ ጠቅላይ ፍ/ቤት ጋብቻ በመፈፀሙ ምክንያት ጋብቻው የሚያመጣው ህጋዊ ውጤት ታውቋል በሚል ግምት የአሜሪካን ዜግነት የመተው ፈቃደኝነት አለ ብሎ በይንዋል።[22]

የውጭ አገር ሴቶች የባሎቻቸውን ዜግነት የማግኘት ፈቃደኝነታቸው ከጋብቻው መፈፀም ሊገመት ይችላል የሚል ተመሳሳይ ክርክርም ሊቀርብ ይችላል። በዚህ ፅሁፍ አቅራቢ አመለካከት ግን ለጋብቻ ፈቃደኛ መሆን ማለት ዜግነት የማግኘትም ሆነ የመተው ፈቃደኝነትን ያመለክታል ብሎ ለማሰብ ያስቸግራል። ጋብቻ መፈፀም በራሱ ህጋዊ ውጤትን የሚያመጣ ህጋዊ ተግባር ነው። ዜግነትን የማግኘትም ሆነ የማጣት ተግባርም እንደዚሁ ፍፁም የተለየ እና ነፃ ህጋዊ ተግባር ሆኖ የተለያዩ ህጋዊ ውጤቶችንም ያስከትላል።

አንድ ሰው የጋብቻን ህጋዊ ውጤቶች ለመቀበል ፍቃደኝነቱን ሰጥቶ፣ በሌላ በኩል ግን አዲስ ዜግነት በማግኘት ወይም የነበረውን ዜግነት በማጣት የሚመጡትን ህጋዊ ውጤቶች ለመቀበል ፍቃደኝነቱን ላይሰጥ ይችላል። በጋብቻ መፈፀም ምክንያት ዜግነት የማግኘት ወይም የማጣት ፍቃደኝነት አለ ብሎ መገመት ግን የሚያሳየው ነገር ቢኖር በመሠረቱ ፍትሃዊ ባልሆነ ሥርዓት ላይ የተመሠረተውንና ጊዜው ያለፈበትን የታማኝነት ፅንሰ ሃሳብ ለመቀጠል የሚደረግ ጥረት መሆኑን ነው።

አድሎአዊና ፍትሃዊ ያልሆነ ህግ ተቀባይነት እንዲኖረው መሞከር የሚያመጣው ችግር ከፍ/ቤቱ የብይን ምክንያቶች ሊታይ ይችላል።

ከላይ በጠቀስነው በማኬንዚና በሄር ክርክር የውጭ አገር ዜጎችን ያገቡ አሜሪካውያን ሴቶች ዜግነታቸውን እንዲያጡ የደነገገውን ህግ አድሎአዊና ፍትሃዊ ያልሆነነው ተብሎ ለቀረበው ክርክር ፍርድ ቤቱ ሲመልስ፤ በጋብቻው ወቅት በሌሎች አገሮች ይታወቅ በነበረው የጋብቻ አንድነት ፅንሰ ሃሳብ መሠረት ሚስትየዋ ወዲያውኑ የባሏን ዜግነት ካልያዘች፣ አሜሪካውያን ሴቶች ያለፈቃዳቸው ዜግነታቸውን እንዲተው የሚያደርገው ህግ፣ አንድ ወጥ ዜግነት እንዲኖር ከሚጥረው ፖለቲካዊ አስተሳሰብ አኳያ ፍትሃዊ ነው ብሏል።[23] በዚያን ጊዜ ይህን አንድ ወጥ ዜግነትን የሚያቀነቅነውን ፖለቲካዊ አስተሳሰብ ለማሳካት ተብሎ፣ እንዴት ያገባች ሴት ዜግነቷን የመምረጥ ነፃነቷ ቢረገጥ ለውጥ አያመጣም ነበር።

ከዚህ አቅጣጫ ሲታይ አንዲት የውጭ አገር ዜጋ በጋብቻ ምክንያት የባሏን ዜግነት መያዟን እንደ አንድ የሌላ አገር ዜግነት ማግኛ መንገድ /ናችራላይዜሽን/ መቀበል አሳሳች ይሆናል። ምክንያቱም ከመወለድ ውጭ የሚገኝ ዜግነትን ለማግኘት ዜግነቱን የሚያገኘው ሰው ተግባርና ፍላጎት ከህጋዊ ሥነ ሥርዓቱ በፊት እንዲኖር ይጠበቃል፤[25] ይህ ደግሞ የሌላን አገር ሰው ያገባች የውጭ አገር ሴት ዜግነቷን ያገኘችበትን መንገድ ሊገልፅ አይችልም። ምክንያቱም የሌላን አገር ሰው ያገባችው የውጭ አገር ሴት ጉዳይ ላይ የጋብቻው ውጤት ወዲያውኑ የመጣ ነው፤ የባሏን ዜግነት እንድታገኝም ሆነ የራሷን ዜግነት እንድታጣ የሴትዮዋ ተግባርም ሆነ ፍላጎት አስፈላጊ አይደለምና። ከ1922 በፊት በአንዳንድ አገሮችና ከዚያም በኋላ እስከ ብዙ ጊዜ በብዙ አገሮች የነበሩት ያገቡ ሴቶችን የሚመለከቱ የዜግነት ህጎች ዋነኛ አላማ አንድ ወጥ ዜግነትን የሚያተኑትነውን ፖለቲካዊ አስተሳሰብ አራምዶ፣ አንድ ወጥ ታማኝነትን ለመጠበቅ እንደነበር ሊታወስ ይገባል።[26] ይህ የፖለቲካ ግብ የተሳካው ያገባችው ሴት ሉዓላዊ የመግለፅ ተፈጥራአዊ መብቷን፣ የባሏን ዜግነት በምትይዝበት የራሷን ዜግነት በምታጣበት ጊዜ እንዳትጠቀምበት በመናቅ ነበር።

በዚህ ረገድ በአውሮፓ አህጉር የነበረው ልምድም ከአሜሪካኑ ልምድ አይለይም ነበር። በአውሮፓ ውስጥም ቢሆን የጋብቻ መፈፀም በራሱ የሚሰትን የዜግነት ማጣት ያስከትል ነበር። ከአንደኛው የአለም ጦርነት በኋላ ወደ 15 የሚሆኑ የአውሮፓ አገሮች ያወጧቸው የዜግነት ህጎች፣ የአገሮቻቸውን ዜጎች ያገቡ የውጭ አገር ሴቶች ሁሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የባሎቻቸውን ዜግነት እንደሚይዙ ደንግገው ነበር።[27]

በአምስቱም የስካንዲኔቪያ አገሮች የውጭ አገር ሴቶች ወዲያውኑ የባሎቻቸውን ዜግነት ይይዙ ነበር። በጀርመንና በጣሊያንም፣ የውጭ አገር ሴቶች ከአገሩ ዜጋ ጋራ ስትጋባ፣ የባሏን ዜግነት ወዲያውኑ እንደምትይዝ ተደንግጓል።

ነገሮች በዚህ ሁኔታ በመቀጠላቸውና ጋብቻ ወዲያውኑ የዜግነት ለውጥ መፍጠሩ በሰፊው የተለመደና በብዙ የአለም አገሮችም ጠንካራ በሆነ መንገድ ስለሚሠራበት በ1923 ዓ.ም. በስቶክሆልም በተደረገው አለም አቀፍ የህግ ኮንፈረንስ

ላይ ፕሮፌዘሮንት ሃማርስኪልድ፤ "በአሁኑ ሁኔታዎች፥ ጋብቻ ወዲያውኑ በሚስት ዜግነት ላይ የሚፈጥረውን ውጤት ለማስቀረት የሚታሰብ ማኛኛያ፥ በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነቱ ዝቅተኛ ይሆናል"[28] ብለዋል። እንዲሁም አንዳንድ የአለም አቀፍ ህግ ባለሙያዎች አንድ ደረጃ በመራመድ፥ የአገባች ሴት ዜግነት የባሏ ዜግነት መሆኑ የአለም አቀፍ ህግ መርህ ነው ብለውም ጠቀመዋል።

- መ -

ከ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ጀምሮ የሴቶች ድርጅቶች ላደረጉት ጥረትና ታዋቂ የሆኑ የዓለም አቀፍ ህግ አዋቂዎች ላቀረቧቸው ሀሳቦች ምስጋና ይግባቸውና ያገቡ ሴቶችን ዜግነት የሚመለከተው ህግ የተለያዩ መንግሥታትን ህግ አውጪ አካላት ትኩረት መሳቡን ቀጥሏል፤ ይህም በተለይ አንደኛው የዓለም ጦርነት ከአበቃ ንኋላ የበለጠ ተጠናክርዋል። ይህ የህግ አውጪዎች ትኩረትም የተገፋፋው በጦርነቱ ወቅት ዜግነት የሌላቸውን ሴቶችና ባሎቻቸውን ባጋጠሟቸው ችግሮች መሆኑ አያጠራጥርም።

በዚህ ረገድ ህግ የማውጣት ርምጃ የወሰደችው የመጀመሪያዋ ሀገር የሩሲያ መንግሥት ነበረች። ጋብቻ በራሱ ብቻ በሚስት ዜግነት ላይ ተፅዕኖ እንደማይኖረው የሚያደርግ ህግ በ1918 አውጥታለች።[30] ሆኖም ግን አንድ ዜግነት የሌላት ሴት አንድ ዜጋ ብታገባና የራሷን ዜግነትም ትታ የባሏን ዜግነት ለማግኘት ብትፈልግ ልታገኝ የምትችልበትን የሥነ ሥርዓት ሁኔታ በብቃት የማያስቀምጥ ህግ የተሟላ ሊሆን አይችልም።

ስለዚህ የአገቡ ሴቶችን ዜግነት በተመለከተ የህግ ማውጣት ሥራን በእርግጥ ያንቀሳቀሰው በአሜሪካ ኮንግረስ የፀደቀው የ1922ቱ ህግ ነበር። በዚህ /ኬብል አክት በመባል በሚታወቀው/ ህግ ውስጥ:-

ሀ/ አንዲት የአሜሪካ ዜግነት የሌላት ሴት ከአንድ የአሜሪካዊ ዜጋ ጋር በመጋባቷ ብቻ የአሜሪካን ዜግነት ወዲያውኑ አታገኝም ነበር፣ ዜግነት ልታገኝ የምትችለው ራሱን በቻለ የዜግነት ማግኛ ሂደት /በናቹራላይዜሽን/ ብቻ ነበር፤ እንዲሁም

ለ/ የአንዲት አሜሪካዊት ሴት ከአንድ አሜሪካዊ ካልሆነ ወንድ ጋር መጋባቷ ብቻውን ዜግነቷን መተዋን ካልገለፀች በስተቀር የአሜሪካ ዜግነቷን አያሳጣትም[31] የሚሉ አንቀጾች ነበሩበት።

ይህ "ኬብል አክት" በመባል የሚታወቀው ህግም ቀስ በቀስ በብዙ መንግሥታት ሕጎች ላይ ተፅዕኖ አድርጎ ነበር። ቤልጅግ /1922/፣ ሩማንያ /1924/፣ ፈረንሳይ /1927/፣ ኖርዌ፣ ስዊድን፣ ዴንማርክ፣ አይስላንድና ፊንላንድ /1924-27/ የአንድ ሴት ዜግነት በባሏ ዜግነት ይወሰናል የሚለውን መርህ በተለያየ ደረጃ የቀየሩ አዳዲስ ሕጎችን አውጥተዋል።[32]

በተጨማሪም ያገቡ ሴቶችን የዜግነት ጉዳይ በተመለከተ ለሚወጡ ብሄራዊ ህጎች መሪ ሊሆኑ የሚችሉ ፅንሰ ሃሳቦችን በማዳበሩ በኩል ዓለም አቀፍ አካላት በንቃት ይሳተፉ የነበሩትም በዚሁ ወቅት አካባቢ ነበር። የአለም አቀፍ ህግ ማህበር በ1922ቱ ኮንፈረንስ በርሱ እምነት ያገባች ሴትን ዜግነት በስምምነት መወሰን እንደሚያስፈልግ፣ ሆኖም እስከተቻለ ድረስ የራሷን ዜግነት የመምረጡን መብት ለራሷ መጠበቅ እንደሚገባ ገልጿል።[33] በነዚያ የአስተሳሰብ መሥመሮች አኳያ የተዘጋጀው ሞዴል ህግም በተከታዩ ዓመት፣ በ1923፣ በስቶክሆልሙ የማሕበሩ ኮንፈረንስ ፀድቋል።

በ1926 የተካሄደው የጋራ ብልፅግና ኮንፈረንስም እንደዚሁ፣ ጋብቻ፣ በሚያገቡት ሴቶች ዜግነት ላይ የሚያስከትለው ውጤት ያሳሰበው መሆኑን ገልጿል።[34]

በመጨረሻም በመንግሥታቱ ሊግ የተቋቋመው የዓለም አቀፍ ህግ አሻሻይ የኤክስፐርቶች ኮሚቴ ያገቡ ሴቶችንም የሚያጠቃልል የዜግነት ህግ መውጣት ያለበት መሆኑን አምኖበታል።

እነዚህ የተለያዩ ጥረቶችም በ1930 ህግ ላይ የፀደቀውን "ከዜግነት ህጎች አለመጣጣም ጋር በተያያዙ የተወሰኑ ጥያቄዎች ላይ የተደረገ ስምምነት" አፍርተዋል።

ሆኖም ግን ይህ ስምምነት ያገባች ሴት የራሷን ዜግነት አራሷ የመምረጥ መብቷን እስከ ማስመለስ ደረጃ ድረስ አልሄደም። የስምምነቱ አንቀፅ 8:-

"የሚስትየዋ አገር ዜግነት ህግ ከአንድ የውጪ ዜጋ ጋራ በመጋባቷ ምክንያት ዜግነቷን የሚያሳጣት ከሆነ ይህ ተግባራዊ የሚሆነው የባሏን ዜግነት ካገኘች ብቻ ነው"[35] ይላል።

ስምምነቱ በመጀመሪያው አንቀጽ፣ አንድ መንግሥት እነማን ዜጎቹ እንደሚሆኑ በራሱ ህግ የመወሰን መብት ያለው መሆኑን የሚገልፀውን ደንብ እንደገና አረጋግጧል። ይህም ደንብ እንዲ ከፀደቀ ከኋላ ጋብቻ ወዲያውኑ የሚፈጥረው ውጤት በተዘዋዋሪ መንገድ እንዲታወቅ መደረጉ የግድ ነበር። አንቀፅ 8፣ 9 እና 11ም በዚህ ዕውቅና ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ስለዚህ፣ በዚህ ረገድ ስምምነቱ በአንቀፅ 1 ከተገለፀው ደንብ መከተላቸው አይቀሬ የሆኑትን የጥንድ ዜግነትንና ሙሉ በሙሉ ዜግነት የማጣትን ችግሮች በመቆጣጠሩ ላይ ራሱን ገድቧል። በመሆኑም ያገቡ ሴቶች የዜግነት ጥያቄ በራሱ እንደጥያቄ አልታየም ነበር፤ ስምምነቱ ባገቡ ሴቶች የዜግነት ህግ ላይ ያተኮረው ሁኔ ጥንድ ዜግነትንና ሙሉ በሙሉ ዜግነት ማጣትን እስካስከተለ ድረስ ብቻ ነበር።

በእርግጥ አጠቃላይ የመንግሥታት ተግባርና ዓለም አቀፍ ስምምነታዊ ህግ "ሚስት በባሏ ሥር በምትቆይበት ጊዜ ውስጥ የእሷ ዜግነት የባሏን ዜግነት ይከተላል" በሚለው ልማዳዊ መርህ ላይ የተመሠረተ እንደመሆኑ የ1930ው ስምምነት ተሳታተፊዎች የሴቶችን መብቶች ዕውቅና ለማሻሻልም ሆነ በዜግነት ጉዳዮች ባልና ሚስት ዕኩል መብት እንዲኖራቸው ለማድረግ አልፈለጉም ነበር።[36] ስለዚህ ኮንፈረንሱ ለብሄራዊ ህግ አወጣጥ ሊረዳ የሚችል ሃሳብ አባሪ ማድረጉን አስፈላጊ አድርጎ ወስዶታል። በኮንፈረንሱ የፀደቀው አራተኛው ሃሳብም:-

1/ "መንግሥታት የልጆችን ፍላጎት ከግምት ውስጥ በማስገባት በዜግነት ጉዳዮች የያዙ እኩልነትን በሕጋቸው ውስጥ ለማስገባትና፣ በተለይም

2/ በመርህ ደረጃ የሚሰጥ ዜግነት ያለፈቃዷ ፈቃድ በጋብቻም ሆነ በባሏ የዜግነት መለወጥ ምክንያት ሊለወጥ እንደማይችል ለመወሰን፣ ይቻላል ወይም አይቻልም የሚለውን ጥያቄ እንዲያጠኑ ኮንፈረንሱ ሃሳቡን ይሰጣል"[37] ይላል።

ስምምነቱ የፀደቀው በጣም ዘግየቶ /በመንግሥታቱ ሊግ ዋና ፀሐፊ ቢሮ የተመዘገበው ጁላይ 1/1937/ እና በጣም በጥቂት አገሮች/ ስምምነቱን ከፈረሙት ከ32ቱ በ11 ብቻ/ ነበር። ይህ ቢሆንም ቅሉ ስምምነቱ እራሱና በተለይም ከስምምነቱ ጋር አባሪ የሆነው ሃሳብ 4/ Recommendation IV/ ከዚያ በኋላ በወጡ የመንግሥታት ሕጎች ላይ ተፅዕኖ ያሳደሩ ይመስላሉ። ስለዚህ በአገር ውስጥ የተወለደችና የውጪ ሰው ያገባች ሴትን በተመለከተ ጥቂት መንግሥታት ዜግነቷን መተዋን በወቅ እስካልገለፀች ድረስ የመጀመሪያውን ዜግነቷን እንደያዘች ለመቆየት እንደምትችል ለማድረግ ፈቃደኝነታቸውን አሳይተዋል። ሆኖም ግን በጣም ከጥቂቶቹ በስተቀር፣ በተግባር ሁሉም መንግሥታት ማለት ይቻላል፣ ከዜጋቸው ጋር ለተጋቡ የውጪ ሴት ለራሳቸው ዜጋ የሰጡትን ያህል መብት ለመስጠት ፈቃደኛ አልነበሩም።[38]

በዚህ መሠረት ከዜጎች ጋር የሚጋቡ የውጪ ሴቶችን ዜግነት በተመለከተ እዚ ፈቀደችም አልፈቀደችም ያገባች ሴት ዜግነት የባሏን ዜግነት ይከተላል የሚለው ጥንታዊ ደንብ መተግበሩ ቀጠለ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የተለያዩ የሴቶች ድርጅቶች፣ የዓለም አቀፍ ህግ ሊቃውንት፣ እንዲሁም አካባቢያዊና ዓለም አቀፋዊ አካላት ያገቡ ሴቶችን የጾታ እኩልነት የሚያረጋግጡ የዜግነት ህግ መርሆዎች እንዲወጡ ለማድረግ ጥረታቸውን ቀጠሉበት።

የ1933ቱ የሞንቴ ቪዲዮ የሴቶች ዜግነት ስምምነት፣ ዜግነትን በተመለከተ ለጾታዎች እኩልነት ዕውቅና የሰጠ የመጀመሪያው በብዙ ሐገሮች መሐከል የተደረገ ስምምነት እንደመሆኑ እዚህ ላይ በተለይ መታየት ይገባዋል።[39] የስምምነቱ አንቀፅ 1 ተዋዋይ አገሮች "ዜግነትን አስመልክቶ በሕጎቻቸውም ሆነ በተግባር ምንም ዓይነት በጾታ ላይ የተመሠረተ ልዩነት አይኖርም፤"[40] የሚለውን አባባል እንዲቀበሉ ያስገድዳቸዋል። በ1945 በተካሄደው በሳንፍራንሲስኮው የዓለም አቀፍ ድርጅት ኮንፈረንስ የተባበሩት መንግሥታት ቻርተር መውጣት ባገቡ ሴቶች የዜግነት ሀግ አዝጋሚ ለውጥ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አሳድርዋል። የቻርተሩ የመጀመሪያው ቁጥር 3ኛው አንቀፅ ሰብዓዊ መብቶችንና መሠረታዊ ነፃነቶችን ለሁሉም የሰው ልጅ ያለምንም የጾታ፣ የዘር፣ ወይም የሃይማኖት ልዩነት ለማዳበርና በትክክል እንዲከበሩ ለማበረታታት ዓለም አቀፍ ትብብርን መፍጠር ከተባበሩት መንግሥታት ዓላማዎች አንዱ እንደሆነ ይገልፃል።[41] የቻርተሩን አንቀጽ 55፣ 56፣ 62፣ 68 እና 76 በተጨማሪ ይመለከቷል።

በ1984 ዓ.ም. ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌ ወጣ። የዚህ ድንጋጌ አንቀጽ 15 እና 16 ከብዙ ሌሎች ጉዳዮች መካከል ማንኛውም ሰው የዜግነት መብት እንዳለው፣ ማንም ዜግነቱን በዘፈቀደ እንደማይነጠቅና ዜግነቱን የመለወጥ መብቱም እንደማይነፈገው፣ ወንዶችና ሴቶች ጋብቻ ሲፈፅሙ በጋብቻ ጊዜና ጋብቻው ሲፈርስ እኩል መብት እንዳላቸው ይገልፃሉ።[42]

በዚህ መካከል በሴቶች ድርጅቶችና ሌሎች ቡድኖች ጫና የሴቶች ክብር ጉዳይ ኮሚሽን የሚባልና በወንዶችና በሴቶች መሐከል እኩልነትን ማስገኘት ዋና ተግባሩ የሆነ አካል በተባበሩት መንግሥታት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ምክር ቤት ተቋቋመ። የኢኮኖሚና ማሕበራዊ ምክር ቤቱ የመጀመሪያ ሃሳብ ለዓለም አቀፍ ሀግ ኮሚሽን የስምምነቱን ረቂቅ የማዘጋጀቱን ኃላፊነት ለመስጠት የነበረ ቢሆንም የሚወስደው ጊዜ ግን ያገቡ ሴቶች የነበሩበት ሁኔታ ሊፈቅድ ከሚችለው ጊዜ አንፃር ሲታይ በጣም እንደሚረዝም ታመነበት። በዚያ ሁኔታ ይህን ረቂቅ ስምምነት የማዘጋጀቱ ሥራ ለሴቶች ክብር ጉዳይ ኮሚሽን ተሰጠው።[43] ከአሥር ዓመታት አካባቢ ጥናትና ውይይት

በኋላም ኮሚሽኑ ያገቡ ሴቶች ስምምነትን ረቂቅ ይዞ ቀረበ። ረቂቅ ስምምነቱም በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ ፀድቆ በኅዳር 28/1957 ለአባል አገሮች ፊርማ ክፍት ተደረገ።[44] ነሐሴ 11 ቀን 1958 ዓ.ም. በሥራ ላይ ዋለ።

ይህ የ1957ቱ ያገቡ ሴቶች የዜግነት ስምምነት፥ ያገቡ ሴቶች ዜግነት ሴቶች እንደ ግለሰብ ካላቸው ክብርና ነፃነት ጋር የሚያያዝ ጥያቄ በመሆኑ ዕውቅና በመስጠት ላይ የተመሠረተ ነው። በመሆኑም ስምምነቱ የጥያቄው ዋና ክፍል የሆነውን ጋብቻ በአገባች ሴት ዜግነት ላይ የሚኖረውን ተፅዕኖ በተቀጥታ ይመለከታል።

የስምምነቱ ቁጥር 1:-
"ማንኛውም የዚህ ውል ተዋዋይ መንግሥት ከዜጎቹ አንዱ ከውጪ አገር ሰው ጋር ጋብቻ ቢፈፅም ወይም የፈፀመው ጋብቻ ቢፈርስ ወይም ጋብቻው ፀንቶ ባለበት ጊዜ ባልየው ዜግነቱን ቢለውጥ የሚስትየዋን ዜግነት ወዲያውኑ እያውከውም በማለት ተስማምቷል" የሚለውን ጠቃሚ አንቀፅ ይዟል /አፅንኦት የተጨመረ/

በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ የተሰበሰበው የዓለም ማሕበረሰብ በዚህ ስምምነት ላይ አንድ ዓይነት አቋም በመያዝ ያገባች ሴት የራሷን ዜግነት ራሷ የመምረጥ መብቷን እውቅላታል። ስምምነቱም ለተሳሚዎቹ መቶ ዓመታት የተደረጉት የሴቶች ድርጅቶችና የዓለም አቀፍ ህግ ሊቃውንት ትግል በድል የመደምደሙ ዋና ምልክት ነው። ስምምነቱ ለፍትሕ በአሸናፊነት መውጣትም ዋና ምልክት ነው በማለት በተጨማሪ መናገር ይቻላል።

ሆኖም ግን ያገቡ ሴቶች የዜግነት ጥያቄ እስከአሁን ድረስም በጥያቄነት በመነሳት ላይ ነው። በ1979 አካባቢ ስምምነቱን ያፀደቁት ተዋዋይ መንግሥታትም ሆኑ ተዋዋይ ያልነበሩ ሆነው ስምምነቱ ውስጥ የገቡት መንግሥታት በጣም ጥቂት ናቸው።[45] ከነዚሁም እንኳን ስምምነቱን ለመተግበር የሚያስችል ብሄራዊ ህግ ያወጡት መንግሥታት ቁጥር ብዙ አይመስልም።

ስምምነቱ በሥራ ላይ ከዋለ ከአምስት ዓመታት በኋላ በተባበሩት መንግሥታት ዋና ፀሐፊ በ1963 የቀረበው ሪፖርት ይህን ጉዳይ ግልፅ ያደርገዋል።[46] በሪፖርቱ መሠረት የመንግሥታት የሕግ ሥርዓቶች በሦስት ዋና ዋና ምድቦች ይመደባሉ።

ሀ/ የመጀመሪያው ምድብ የሚስት ዜግነት የባሏን ዜግነት ወዲያውኑ የሚከተልበትን የሀግ ሥርዓቶች ያካትታል። ማለትም ጋብቻ እራሱ፣ የጋብቻ መፍረስ እና ጋብቻው ፀንቶ በአለበት ጊዜ ባልየው ዜግነቱን ሲለውጥ በሚስት ዜግነት ላይ ቀጥተኛ የሆነ ውጤት ያስከትላል። የ1930ው የኢትዮጵያ የዜግነት ሀግ በዚሁ ሥር እንደሚገባ በሪፖርቱ[47] ተመልክቷል። ኢትዮጵያን፣ ጣሊያንን፣ አውስትሪያን፣ ግሪክን፣ ኔዘርላንድን፣ ስዊዘርላንድን፣ ፖርቹጋልንና ቱርክን ጨምሮ ወደ ሃያ ሰባት መንግሥታት በዚህ ምድብ ሥር ይወድቃሉ።

ለ/ ሁለተኛው ምድብ ደግሞ ጋብቻ የአንዲትን ባዕድ ሚስት ዜግነት ወዲያውኑ የሚነካበትን ሁኔታ የሚከተሉ የሀግ ሥርዓቶችን ያጠቃልላል። ሆኖም ገን ሙሉ በሙሉ ዜግነት ማጣትንና ጥንድ ዜግነትን ለማስወገድ በማሰብ የቤተሰብ አሀዳዊነት መርሀን ከባልየው መንግሥት የሀግ አንቀጾች ጋር እንዲስማማ በማድረግ በመጠኑ ለውጥ ተደርጎበታል። ቻይናን፣ ቤልጅግን፣ ቱኒዝያን፣ ቦሊቪያንና ካሜሩንን ጨምሮ ወደ 13 መንግሥታት በዚህ ምድብ ሥር ይወድቃሉ።

ሐ/ የመጨረሻው ምድብ ደግሞ ጋብቻ በአንዲት የውጪ አገር ሚስት ዜግነት ላይ፣ ካለእራሷ ፍቃድ፣ ምንም ተፅዕኖ እንደሌለው የሚደነግጉ የሀግ ሥርዓቶችን ያካትታል። ከነዚህም ውስጥ በግምት 24ቱ መንግሥታት ባዕዷ ሚስት የባሏን ዜግነት የማግኘት መብት እንዳላት ብቻ ዕውቅና ይሰጣሉ፤ ወደ 24 መንግሥታት ዜግነት ለማግኘት የሚያስፈልጉትን ጉዳዮች ቀላል አድርገው ሲያቀርቡ ሌሎች ወደ 12 የሚሆኑ መንግሥታት ደግሞ ጋብቻ በባዕዷ ሚስት ዜግነት ላይ ምንም ዓይነት ተፅዕኖ እንዳለው ዕውቅና አይሰጡም።[48]

የአንዲት ዜጋ የሆነች ሴት ከውጪ ባል ጋር መጋባትን በተመለከተ ያለው ሁኔታ ግን በጣም የተለየ ትርዕ የያዘ ነው።[49] ስድስት መንግሥታት ባዕድ ባል ያገባችን ሴት ዜጋ ወዲያውኑ ዜግነቷን ያሳጧታል፤ የኢትዮጵያ የዜግነት ህግም፥ እንደሪፖርቱ አባባል፥ የሚጠቃለለው በዚሁ ምድብ ሥር ነው። ሆኖም ግን አንዲት ኢትዮጵያዊት የኢትዮጵያዊነት ዜግነቷን የምታጣው የባሏን ዜግነት ካገኘች ብቻ ነው። ወደ አሥራ ሰባት መንግሥታት ደግሞ የውጪ አገር ወንድ ያገባች ሴት ዜጋ የባሏን ዜግነት ማግኘት ወዲያውኑ ዜግነቷን የሚያሳጣ ህግ አላቸው። ወደ ሰባ መንግሥታት ግን ሴቶች ዜጎቻቸው የውጪ አገር ወንዶችን ቢያገቡም ዜግነታቸውን ይዘው የመቆየት መብታቸውን ይጠብቁላቸዋል።

ከዚህ እንደሚታየው፥ ምንም እንኳን የ1957ቱ ስምምነት ራሱን የቻለ ድል ቢሆንም የስምምነቱ ትርዕና ይዘት በሁሉም መንግሥታት ዘንድ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊነትን እንዲያገኝ ብዙ መደረግ ያለበት ነገር አለ።

- ሠ -

ጋብቻ ባገባች ሴት ዜግነት ላይ ከሚኖሩት ተፅዕኖዎች ውስጥ አንዱ በውጂታም ይሁን በግጂታ ሴትዮዋ ጥንድም ብቻ ሳይሆን ብዙ ዜግነት የማግኘት ዕድሏን መጨመሩ ነው። አብዛኛውን ጊዜ መንግሥታት ዜጎቻቸው እነማን እንደሆኑ ለመወሰን በሚከተሏቸው የተለያዩ መርሆች መካከል ግጭት ሲፈጠር ጥንድ ዜግነት ለማንኛውም ሰው ይከሰታል። ስለዚህ አንድ አሜሪካ ውስጥ ከኢትዮጵያውያን ወላጆች የተወለደ ሰው የእንግሊዝን ዜግነት ቢያገኝ ሰውየው ጥንድ ብቻ ሳይሆን ብዙ ዜግነት ይኖረዋል ማለት ነው። ይህ የሆነበት ምክንያትም ኢትዮጵያ የምትከተለው መርህ ዩስ ሳንግዊኒስ የሚለውን ሲሆን አሜሪካ ግን ዩስ ሶሊ የሚለውን መርህ ስለምትጠቀም ነው። የእንግሊዝ የዜግነት መስጫ ህግም አንድ ሰው የእንግሊዝን ዜግነት ለማግኘት የመጀመሪያ ዜግነቱን እንዲለቅ አይጠይቅም።[50] ስለዚህ አንዲት አሜሪካ ውስጥ የተወለደችና የእንግሊዝን ዜግነት ያገኘች ኢትዮጵያዊት ሴት የጀርመን ዜጋ ብታገባ /የጀርመን ህግ የጀርመን ዜጋ ላገባች የውጪ ሴት የጀርመን ዜግነት ወዲያውኑ

ይሰማል፥[51]/ ሴትዮዋ የአራት መንግሥታት ዜግነት ባለቤት ሆና ታርፈዋለች ማለት ነው።

ጥንድ ዜግነት የሚፈጠረው ጁስ ሳንጊኒስ እና ጁስ ሶሊ የተባሉት መርሆች በሚጋጩበት ሁኔታ መንግሥታት በመጠቀማቸው ምክንያት ብቻ ሳይሆን መንግሥታት ዜጎቻቸው ራሳቸውን ከዜግነት እንዳያገሉሉ /ዜግነታቸውን እንዲተው/

ስለማይፈቅዱላቸውና ጥቂት መንግሥታት ደግሞ የራሳቸውን ዜግነት ለውጪ ሰዎች ከመስጠታቸው በፊት ሰዎቹ ከቀድሞ ዜግነታቸው ወይም ተገዢነታቸው መልቀቂያ እንዲያቀርቡ ስለማይጠይቋቸውም ጭምር ነው።[52]

ጋብቻ ባገቡ ሴቶች ዜግነት ላይ ለውጥ የማስከተሉ ሁኔታ የጥንድ ወይም የብዙ አገር ዜግነት የመከሰትን መጠን ይጨምረዋል። በዚህ ጽሁፍ መጀመሪያና ወደ በኋላ ላይ የተጠቀሰው የአቤት ባይዋ ጉዳይ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው። አቤት ባይዋ ዜጋ በሆነችበት በሶቭየት ሕብረት የዜግነት ህግ፥ ጋብቻ የሶቭየት ሴትን ዜግነት አይለውጠውም፤[53] የኢትዮጵያ የዜግነት ህግ ግን ከአንድ የኢትዮጵያ ዜጋ ጋር ሕጋዊ ጋብቻ ለፈፀመች የውጪ አገር ሴት የኢትዮጵያን ዜግነት ይሰጣታል። እዚህ ላይ እንደተመለከተው የኢትዮጵያ የዜግነት ህግ የተመሠረተው የአንዲት የውጪ አገር ዜግነት ያላት ሚስት ዜግነት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የባሏን ዜግነት ይከተላል በሚለው ጥንታዊ መርህ ላይ ሲሆን፥ በሶቭየት ህብረት ህግ ግን አንድ ኢትዮጵያዊ ዜጋን ያገባች የሶቭየት ሴት የግድ ጥንድ ዜግነት ይኖራታል።

አንድ ሰው ያለውን ጥንድ ወይም የብዙ አገር ዜግነት ዜግነታቸውን ከያዘው ከአንዱ መንግሥት ወደ ሌላው በመንቀሳቀስ ህጋዊ ግዴታዎቹን ላለመወጣት፥ ወይም ጥቅሞች ለማግኘት ሊጠቀምበት ይችላል።

በሌላ በኩል ደግሞ ጥንድ የብዙ አገር ዜግነት ያለው ሰው ግዴታዎቹን ዜጋ በሆነባቸው መንግሥታት የተለያዩ የህግ ሥርዓቶች ውስጥ ሁሉ እንዲወጣ ሊገደድ

ይችላል። የውትድርና አገልግሎት የመስጠትና ግብር የመክፈል ግዴታዎች አንድ
ባለጥንድ ወይም የብዙ አገር ዜግነት ያለው ሰው ዜጋቸው በሆነባቸው መንግሥታት
ሁሉ እንዲፈፅም በአብዛኛው የሚገደድባቸው ዋና ዋና ምሳሌዎች ናቸው። ይህም
የሰውየውን ህይወት ከባድ ሊያደርገው መቻሉ ግልፅ ነው።

ሆኖም ግን ጥንድ ወይም የብዙ አገር ዜግነት ባለው ሰው ላይ የሚያጋጥሙ
ዐውነተኛ ችግሮች የሚከሰቱት እንዲህ ዓይነቱ ሰው በአንድ መንግሥት በደል
ሲደርስበት ነው። ይህ ሲፈጠር የተበደለው ሰው እራሱ በደል በደረሰበት መንግሥት
ላይ ዓለም አቀፍ አቤቱታ ሊያቀርብ አይችልም፤ ምክንያቱም ግለሰቦች የዓለም አቀፍ
ህግ ተገዢዎች /subjects/ ባለመሆናቸው ዓለም አቀፍ ቦታ የላቸውም የሚል
አጠቃላይ የሆነ ስምምነት በመኖሩ ነው።[54] የተበደለው ሰው በበደለው መንግሥት ላይ
ዓለም አቀፍ አቤቱታ ሊያቀርብ የሚችለው ዜግነት ከያዘባቸው ከአንዱ ወይም
ከሌላው መንግሥት ዲፕሎማሲያዊ ከብካቤ እንዲደረግለት በመጠየቅ ብቻ ነው።
ዜግነት በአንድ ሰውና በአንድ መንግሥት መካከል የሚፈጠር፣ የዚያ መንግሥት
ሥልጣን ከክልሉ ውጪ እንዲሄድና የመንግሥቱ ህግም በግለሰቡ ላይ እንዲሠራ
የሚያደርግ ህጋዊ ግንኙነት እንደመሆኑ ባለጥንድ ወይም የብዙ አገር ዜግነት ያለው
ሰው የሥልጣንና የዲፕሎማሲያዊ ከብካቤ ጥያቄ ይህ ሰው ዜጋቸው የሆነውን የሁሉም
መንግሥታት ፍላጎት ይነካል። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ ጥንድ ወይም የብዙ
አገር ዜግነት ላለው ሰው የሥልጣንና የዲፕሎማሲያዊ ከብካቤ
የመስጠት ጥያቄ ግጭት ጉዳዩ በሚመለከታቸው መንግሥታት መሐከል መከሰቱ
የግድ ነው።

ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ዜግነት ያለው ሰው ዲፕሎማሲያዊ ጥበቃ
ይደረግለት ዘንድ በሀገሮች የሚቀርቡ ጥያቄዎች እንዴት ይፈታሉ?

እነዚህ ጥያቄዎች አለም አቀፋዊ ባህሪ ያላቸው እንደመሆኑ መጠን የሚፈቱትም
በአለም አቀፍ ልማዳዊ ህግ በአለም አቀፍ ስምምነቶች ነው።

በአሁኑ ወቅት እያንዳንዱ ሀገር የዜጎቹን ማንነት የመወሰን ሥልጣን ያለው መሆኑ ተቀባይነት ያለው የአለም አቀፍ ህግ መርህ ሆንዋል። የዚህ መርህ ተቀባይነት በቋሚው አለም አቀፍ ፍርድ ቤት /ፐርማነንት ኮርት ኦፍ ኢንተርናሽናል ጀስቲስ/ እንዲሁም በአሁኑ አለም አቀፍ ፍርድ ቤት[57] ውሳኔ በተሰጣቸው በርካታ ጉዳዮች ላይ ተረጋግጧል። ይኸው መርህ በ1930ው የህግ ኮንቬንሽንም ተቀባይነትን አግኝቷል፤ በውስጥ ህጎች አማካይነት የዜጎቹን ማንነት መወሰን የእያንዳንዱ ሀገር ሥልጣን ነው።[58]

አለም አቀፉ ፍርድ ቤት በኖትቦህም ጉዳይ ከደረሰባቸው ግኝቶች በሃሳብ የሚለዩት ሽን ፓንሁይሰና ጆሴፍ ኤል ኩንዝን የመሳሰሉት ጸሐፍት እንኳ እያንዳንዱ

ሀገር ላለው የዜጎቹን ማንነት የመወሰን መብት አለም አቀፍ ህግ እውቅና የሚሰጥ በመሆኑ ላይ ይስማማሉ።[59] ስለዚህም፣ አንድ ሀገር በውጪ የሚኖሩ ዜጎቹን በተመለከተ በዜጎቹ ላይ ያለውን የዳኝነት ሥልጣን ወይም ሉአላዊነትን እስከምን ድረስ ሊያሰፋ እንደሚችል በዚያው ሀገር ህግ የሚወሰን ነው።[60]

እንግዲህ እያንዲንዱ ሀገር በአለም አቀፍ ህግ መሠረት በራሱ የውስጥ ህግ እየተመራ የዜጎቹን ማንነት የመወሰን መብት ካለው ሌሎች ሀገሮችም ይህንኑ ውሳኔ የመቀበል ግዴታ አለባቸው ማለት ነው። በእርግጥ ከላይ የተጠቀሰው የሕግ ኮንቬንሽን በአንቀጽ 1 እንደሚያስቀምጠው እያንዳንዱ ሀገር የዜጎቹን ማንነት የሚወስንበት የውስጥ ህግ /የዜግነት ህግ/ "ከአለም አቀፍ ኮንቬንሽኖች፣ ከአለም አቀፍ ልማድ፣ እንዲሁም ዜግነትን በተመለከተ አጠቃላይ ተቀባይነት ካላቸው የህግ መርሆች ጋር የሚጣጣም እስከሆነ ድረስ በሌሎች ሀገሮች ዘንድ ተቀባይነት ማግኘት አለበት።"

የዜግነትን ጉዳይ በተመለከተ ከላይ የተጠቀሰው አንቀጽ 1 የአንድ ሀገር የህግ አውጭው አካል የሥልጣን ክልል ከዚህም ጋር የሕጉ አስገዳጅነት በዚያው ሀገር የግዛት ክልል ውስጥ የተወሰነ ነው ከሚለው መርህ ጋር የሚስማማ ነው።

ከዚህ በማያያዝ "ምንም ዓይነት አለም አቀፍ ውል ወይም ሌላ ዓይነት አለምአቀፍ ግዴታ በሌለበት ሁኔታ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ከኢትዮጵያ ህግ በቀር በሌላ ህግ ለመዳኘት አሻፈረኝ ለማለት ይችላሉ"[62] ቢባል ስህተት አይሆንም።

በሌላ አነጋገር አንድ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤት ምንጩ ከሶቪየት ለሆነ አንድ ግለሰብ በኢትዮጵያ የዜግነት ህግ መሠረት የኢትዮጵያ ዜግነት ለመስጠት አሻፈረኝ ማለት አይችልም። ለዚህም በኢትዮጵያና በሶቪየት የዜግነት ሕጎች መካከል ያለው ልዩነትና በዚሁም ሳቢያ ግለሰቡ ዜግነት ሊኖረው መቻሉ ለክልከላው እንደምክንያት ሊቆጠር አይችልም።[63] የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ከኢትዮጵያ ህግ ጋር የማይጣጣመውን የሶቪየት ህግ በኢትዮጵያ ውስጥ በሥራ ላይ የማዋል ግዴታ የለባቸውም። ስለዚህ ፍርድ ቤቶቹ የሶቪየትን ህግ ከግምት ውስጥ ሳያስገቡ ግለሰቡ ኢትዮጵያዊ ዜግነት እንዳለው ሊወስኑ ይችላሉ። የኢትዮጵያ የዜግነት ህግ ጣምራ ዜግነትን የማይቀበል በመሆኑ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች አንድን የውጭ ሀገር ዜጋ፣ በኢትዮጵያ የዜግነት ህግ መሠረት ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው ከሆነ እንደውጭ ሀገር ዜጋ ሊመለከቱት አይችሉም።

ከዚህ በላይ የተመለከተው በሄግ ኮንቬንሽን አንቀጽ 3 ሥር የተደነገገው መርህ ነው። ይኸው አንቀጽ "በዚህ ኮንቬንሽን የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ዜግነት ያለው ሰው የዜግነት መብቱን ያገኘበት የእያንዳንዱ ሀገር ዜጋ ሆኖ ሊቆጠር ይችላል"[64] ይላል።

አንድ ግለሰብ ጣምራ ዜግነት በሚኖረው ጊዜ ለግለሰቡ የዜግነት መብት በሰጡት ሁለት ሀገሮች መካከል አንዱ ከሌላው ተቃራኒ በሆነ ሁኔታ ለግለሰቡ ዲፕሎማሲያዊ ከለላ /ጥበቃ/ ሊሰጥ አይችልም። ይህ መርህ አለም አቀፍ ፍርድ ቤት በኖተቦህም ጉዳይ ላይ በሰጠው ውሳኔ ተቀባይነቱ የተረጋገጠ ከመሆኑም ባሻገር በሄግ ኮንቬንሽን አንቀጽ 4 ሥር ተደንግጓል። ስለዚህ "አንድ ሀገር ጣምራ ዜግነት ላለው ግለሰብ፣ ግለሰቡ ሁለተኛ ዜግነቱን ላገኘበት ሀገር ተቃራኒ በሆነ ሁኔታ ዲፕሎማሲያዊ ጥበቃ ሊሰጥ አይችልም።[65]

ሶስተኛ ሀገሮችን በተመለከተ የሀገሮች አሠራር ካንዱ ወደ ሌላው ሊለያይ ይችላል። ለምሳሌ በብሪታኒያ እንግሊዛዊ ዜግነት ያገኘ ሰው ከተድሞ ዜግነቱ በሀጋዊ መንገድ ባልተላቀቀበት ሀገር ከልል ውስጥ ካልሆነ በቀር በሌላው ቦታ ሁሉ በእንግሊዝ ዜግነት ይታወቃል።[66] ይሁን እንጂ ሌሎች ሀገሮች ተጨማሪ የሌላ ሀገር ዜግነት ያለውን ግለሰብ እንደ እንግሊዛዊ ላይቀበሉት የችላሉ። ይህን አስመልክቶ አንድ እንግሊዛዊ የአለም አቀፍ ህግ ምሁር ሀሳብ ሲያቀርቡ "በዚህ ትላይ ... ላይ ከአለም አቀፍ ዉሉች ከሚመነጩ ግዴታዎች ባሻገር ሀገሮች ሊከተሉት የሚገባው ትክክለኛው መመዘኛ ግለሰቡ ለመጨረሻ የመረጠውን ሀገር ዜግነት ማወቅ ነው" [67] ብለዋል።

በዚህ ነጥብ ላይ የሄጉ ኮንቬንሽን በይበልጥ ተጨባጭ የሆነ መመዘኛ የወሰደ ይመስላል። በኮንቬንሽኑ አንቀጽ 5 ሥር የሚከተለው ሰፍርዋል፤

"በአንድ በሦስተኛ ሀገር ውስጥ ከአንድ በላይ ዜግነት ያለው ሰው የአንድ ሀገር ዜግነት ብቻ እንዳለው መቆጠር አለበት። ... ሶስተኛው ሀገር ግለሰቡ ካለው የተለያየ ዜግነት ውስጥ ግለሰቡ አዘውትሮና በዘላቂነት የሚኖርበትን ሀገር ዜግነት ወይም እንደሁኔታው ግለሰቡ በይበልጥ ቅርበት ያለው መስሎ የሚታየውን ሀገር ዜግነት በክልሉ ውስጥ ሙሉ በሙሉ መቀበል አለበት።"[68]

ሁለት ወይም በላይ የሆኑ ሀገሮች የእነርሱ ዜግነት ላለው ግለሰብ ዲፕሎማሲያዊ ጥበቃ ለመስጠት ያላቸውን መብት አስመልክቶ የሚፈጠር አለመግባባት ብዙውን ጊዜ እጅግ አወዛጋቢ ይሆናል። በተመሳሳይ ሁኔታ ሚስተር ኖተቦህም ለተባለ ግለሰብ ዲፕሎማሲያዊ ጥበቃ ወይም ከለላ መስጠትን አስመለከቶ በጓቴማላና ሊክተንስታይን መካከል በተነሳው ውዝግብ አለም አቀፍ ፍርድ ቤት ከግለሰቡ ጋር ቀጥተኛና ግልፅ የሆነ ግንኙነት /ጀኑዊን ሊንክ/ ያለው ሀገር ዲፕሎማሲያዊ ጥበቃ የመስጠት መብት አለው በማለት ወስኖዋል።[69]

ይህ የ "ቀጥተኛና ግልፅ ግንኙነት" /ጀኑዊን ሊንክ/ ፅንሰ ሃሳብ በብዙ የአለም አቀፍ ህግ ምሁራን ዘንድ ተቀባይነትን አላገኘም። በርግጥም ይህ ፅንሰ ሃሳብ በሄግ

ኮንቬንሽን አንቀጽ 3 ውስጥ ከተጠቀሰውና በየሀገሮቹ የውስጥ ህግ መሠረት አንድ ሰው የሁለት ወይም ከዚያ በላይ ሀገሮች ዜግነት በሚኖረው ጊዜ ከግለሰቡ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ኖረውም አልኖረው እያንዳንዱ ሀገር ግለሰቡን እንደራሱ ዜጋ ሊቆጥረው ይችላል ከሚለው መሠረታዊ መርህ ጋር የሚቃረን ነው። የ "ጁስ ሳንጉዊን" መርህን የሚከተል አንድ ሀገር ለምሳሌ ከዜጎቹ የተወለደ ማንኛውንም ግለሰብ ከዚህ ቀደም ሀገሩን ፊቱም አይቶ የማያውቅ እንዲሁም በግለሰቡና በሀገሩ መካከል ምንም ዓይነት ግንኙነት የሌለው ቢሆንም እንኳ እንደራሱ ዜጋ ይቆጥረዋል። በዚህ ረገድ ሻን ፓንሁይሰም ሆነ ጂ.ኤል. ኩንዝ "የቀጥተኛና ግልፅ ግንኙነት" መርህ /ጂኑዊን ሊንክ/ ከአለም አቀፍ ልማዳዊ ህግ ውስጥ የሚመደብ መሆኑን የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ እንደሌለ አበክረው ተከራክረዋል።[70] ይልቁንም በአንድ ሀገርና በአንድ ግለሰብ መካከል አነስተኛም ቢሆን ግንኙነት እስካለ ድረስ ግለሰቡ የዚሁ አገር ዜጋ ነው የሚል አስተያየት ይሰነዝራሉ።

ይሁን እንጂ አለም አቀፍ ፍርድ ቤት በኖተቦህም ጉዳይ ላይ የጠቀሰው የቀጥተኛና ግልፅ ግንኙነት /ጂኑዊን ሊንክ/ መርህ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሀገሮች የእነርሱን ዜግነት ለያዘ ግለሰብ የሚሰጡትን ዲፕሎማሲያዊ ጥበቃ አስመልክቶ በሀገሮች መካከል ለሚነሳው ክርክር እንደመፍትሄ የሚያገለግል መርህ መሆኑ አጠቃላይ ስምምነት የተደረሰበት ነው።[71]

ጣምራ ዜግነትና ዜግነት አልባነት የመሳሰሉ ሁኔታዎች አለም አቀፍ ማህበረሰብ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊያስወግዳቸው የማይችል ችግሮች ይመስላሉ። የሀገሮች የዜግነት ሕጎች አለመመሳሰልና እንዲሁም ከዜግነት መላቀቅን የሚገዙት ሕጎች መለያየት ችግሮቹ ወደፊትም በተደጋጋሚ እንዲከሰቱ ያደርጋል። ጦርነትና አብዮት /ለውጥ/ የመሳሰሉ ክስተቶች አንድን ሀገር የተወሰነ የግዛት ክልል ሊያሳጡ ወይም የዚያን ሀገር ጠቅላላ መበታተን ሊያስከትሉ ይችላሉ። ይህ በበኩሉ ደግሞ ጥቂቶች ጭርሱን ዜግነት አልባ /ዜግነት የለሽ/፣ ሌሎች ደግሞ ከአንድ በላይ ዜግነት ያላቸው የሚሆኑበትን ሁኔታ ይፈጥራል።[72]

በዜግነት ሕጎች መካከል ያለው ግጭት ከ "ብሄራዊ አገር" /ኔሽን ስቴትስ/ መርህ ማቆጥቆጥ ጋር የተከሰተ አዲስ ችግር በመሆኑ ለችግሩ አግባብ ያላቸው ኮንቬንሽኖችና ልማዳዊ የአለም አቀፍ ህግ መርሆች እስኪዳብሩ ድረስ ረዘም ያለ ጊዜ የሚወስድ ይመስላል። መናልባት የአውሮፓ ኢኮኖሚ ማኅበረሰብን የመሳሰሉ ልዕለ መንግሥታዊ /ሱፐራናሽናል/ ድርጅቶች ወደ ከፍተኛ የውህደት ደረጃ መድረስ የአንድ ግለሰብ የትውልድ ቦታ እንዲሁም የወላጆች ማንነት ከግምት ውስጥ ወደ ማይገባበት አዲስ ዓይነት አሠራር ሊያመራ ይችላል። ከዜግነት ጋር ተያይዞ የሚከሰተው ችግር ሀገሮች ስለሉአላዊነታቸው ያላቸው አመለካከት በአዲስ አመለካከት ሲተካ ብቻ የሚወገድ ይመስላል።

እስከዚያ ድረስ ግን አለም አቀፍ ህግ ለጣምራ ዜግነትና ዜግነት አልባነት መኖር እውቅና እንደሰጠ ይቆያል። የ1930 ዓ.ምቱ የሄግ ጉባዔ እንዲሁም በጉባዔው የፀደቀው ኮንቬንሽን የጣምራ ዜግነትና ዜግነት አልባነት ክስተቶችን ይቀበላል። ነገር ግን ጉባዔውም ሆነ ኮንቬንሽኑ የችግሮቹን ምልክቶች እንጂ መንስኤያቸውን አልመረመሩም። ይህም የሆነበት ምክንያት ሀገሮች የዜጎቻቸውን ማንነት የመወሰን መብት ያቀዳጃቸውን ሉአላዊነት ለድርድር ለማቅረብ ፈቃደኛ ሆነው ባለመገኘታቸው ነው።[73]

ዜግነት አልባነትና ጣምራ ዜግነት በግለሰቦች ላይ ውስብስብ ችግሮች ከማስከተላቸውም በላይ አልፎ አልፎም በሀገሮች መካከል ግጭቶችን ይፈጥራሉ። ስለዚህ እነዚህን ክስተቶች ማስወገድ አስፈላጊ ነው። ይህን ከግብ ለማድረስ ... ጆሴፍ ኤል ኩንዝ በ1960 ዓ.ም. ከሰነዘረው ሃሳብ የተሻለ አማራጭ ያለ አይመስልም። ይህንኑ አስመልክቶ ኩንዝ የሚከተለውን ብሏል፤

"... አለም አቀፍ ህግ ከዜግነት ጋር ተያይዞ የሚፈጠረውን ችግር ሥርዓት ባለው መንገድ ሊፈታው ይገባል። ይህም የሚሆነው ችግሩን የመፍታት ሥልጣንና ኃላፊነት ለሀገሮች አሳልፎ በመስጠት ሳይሆን የዜግነትን አሰጣጥም በተመለከተ መብትና ግዴታዎችን የሚደነግጉ አንድ ወጥ መርሆችን በማውጣት ነው። ይህም

ቢሆን በራሱ በቂ አይደለም። ይህንኑ ጉዳይ በተመለከተ አለም አቀፍ ውል ቢፈረምና ቢፀድቅም እንኳን በቋንቋዎችና በየሀገሮቹ ፍርድ ቤቶች በሚሰጡ ትርጓሜዎች ልዩነት ሳቢያ ሌላ ግጭት መፈጠሩ አይቀሬ ነው። ስለዚህ አለም አቀፍ ጢሉን አንድ ወጥ በሆነ መንገድ ሥራ ላይ የሚያውል አለም አቀፍ የዜግነት ፍርድ ቤት በተጨማሪ ማቋቋም ያስፈልጋል።"[74]

ነገር ግን ይህ አመለካከት ሰፊ ተቀባይነትን ከማግኘቱ በፊት ረዘም ያለ ጊዜ ይጠይቃል። እስካሁንም ድረስ ሀገሮች በውስጥ ሕጎቻቸው መሠረት ያላቸውን የዜጎቻቸውን ማንነት የመወሰን ሰፊ ሥልጣን እንደያዙ ናቸው። የዜጎቻቸውን ማንነት በመወሰኑ ሂደት የአለም አቀፍ ውል ገደታዎችን ጨምር የሚከተሉዋቸው መመሪያዎች አሉዋቸው። በዚህም ለዜጎቻቸው ጣምራ ዜግነት ሊሰጡ የሚችሉና ዜግነት አልባነት ሊያስከትሉ የሚችሉ ድንጋጌዎችን ከሕጎቻቸው ውስጥ ያስወግዳሉ። ከ1930 የኢትዮጵያ የዜግነት ሕግ አንቀጽ 4ን የመሳሰሉ ድንጋጌዎች እንደዚህ ባሉ ግንዛቤዎች ላይ የተመሠረቱ ናቸው። አንዲት ኢትዮጵያዊት ኢትዮጵያዊ ያልሆነ ባልዋን ዜግነት ብታገኝ ወዲያውኑ ኢትዮጵያዊ ዜግነትዋን ታጣለች። ይህ ሴቲቱ በአንድ ጊዜ ኢትዮጵያዊ ዜግነትና የባልዋን ዜግነት የምታገኝበትን ሁኔታ ያስወግዳል። በሌላ በኩል የባልዋ ሀገር የዜግነት ህግ የባልዋን ዜግነት የማይሰጣት ከሆነ ወዲያውኑ ኢትዮጵያዊ ዜግነትዋን ትይዛለች። ይህ አንዲት ከውጭ ሀገር ዜጋ ጋር ጋብቻ የፈፀመች ኢትዮጵያዊት የባልዋን ዜግነት ሳታገኝ ኢትዮጵያዊ ዜግነት እንዳታጣና በዚሁም ሳቢያ ዜግነት አልባ የምትሆንበት ሁኔታ እንዳይፈጠር ለማድረግ የታቀደ ነው።

ሀገሮች እነዚህን መርሆች በሕጎቻቸው ውስጥ ሊያስገቡዋቸው ይችላሉ። ነገር ግን በዚህ ረገድ በሌሎች ሀገሮች የውስጥ ህግ ላይ ምንም ዓይነት ተፅእኖ ማሳደር አይችሉም። በሌላ አነጋገር ሌሎች ሀገሮች የድርብ ዜግነትን መከሰት የሚያመቻቹ ህጎችን ከማውጣት እንዲታቀቡ ማድረግ አይችሉም። ይህም በዜግነት ሕጎቻቸው ውስጥ ጋብቻ በሴቶች ዜግነት ላይ ምንም የተለየ ውጤት አያስከትልም ብለው

በሚደነገጉ ሀገሮች ውስጥ ሊከሰት የሚችል ሲሆን የሶቪየት ህብረት የዜግነት ህግ ከነዚህ አንዱ ነው።[75]

እንዲህ ባለው ሁኔታ አንዲት ሴት ፍላጎት ቢኖራትም እንኳ የባሏዋን ዜግነት ማግኘት አትችልም። ስለዚህ አንዲት የሶቪየት ዜጋ አንድ ኢትዮጵያዊ ብታገባ ጥምር ዜግነት ይኖራታል። ነገር ግን አንዲት የዮርዳኖስ ዜጋ አንድ የሶቪየት ዜጋ ብታገባ ምንም ዜግነት አይኖራትም ማለት ነው። ምክንያቱም በዮርዳኖስ ህግ መሠረት ከውጭ ዜጋ ጋር ጋብቻ የፈፀሙ ዮርዳኖሳዊት ወዲያውኑ ዜግነትዋን የምታጣ ሲሆን[76] በሶቪየት ህግ መሠረት ደግሞ ዜግነትዋ በጋብቻ የተነሳ የማይለወጥ በመሆኑ ነው።[77]

የየሀገሮቹን የውስጥ ሕግጋት የሚወስኑት መሠረተ ሀሳቦችና ግንዛቤዎች የተለያዩ በመሆናቸው አንድ አገር የሀገሩን ነዋሪነትና የሚያስከትለውንም ውጤት በቀላሉ ከሌሎች ሀገሮች ሕጎች ጋር የሚስማማ እንዲሆን ለማድረግ አይችልም። ይህንንም ለማድረግ ከአለም አቀፍ ውል ከሚመነጩ ግዴታዎች በቀር ሞራላዊም ሆነ ሕጋዊ ግዴታ የለበትም። ይሁን እንጂ ሀገሮች ዜግነትን በተመለከተ ሰፊ ተቀባይነት ካላቸው መርሆች ራሳቸውን ነፃ ማድረግ ይችላሉ ማለትም አይደለም።[78]

ከዚህ በላይ በሚገባ የተብራሩትና ዜግነትን በተመለከተ በሰፊው የሚሠራባቸው መርሆች በይበልጥ ግልፅ ይሆኑ ዘንድ በአጭሩ ይታያል።

ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ዜግነትን አስመልክቶ ለተደረገ አለም አቀፍ ውል ተዋዋይ የሆነ ሀገር የውሉን ድንጋጌዎች ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ አለበት። የዚያው ሀገር ፍርድ ቤቶችም እንዲሁ ድንጋጌዎችን በሥራ ላይ ማዋል አለባቸው። የዚህ ዓይነቱን አለም አቀፍ ውል ድንጋጌዎች አለማክበር በአለም አቀፍ ህግ ሥር ያለ ማንኛውንም ዓይነት ቅጣት ሊያስከትል ይችላል።

ከአለም አቀፍ ውል የሚመነጭ ምንም ዓይነት ግዴታ በሌለበት ሁኔታ የዜግነት ጥያቄ በሀገሮች የውስጥ ህግ መሠረት ይፈታል። በአለም አቀፍ ህግ ዘንድ አንድን

ግለሰብ በዜግነት መቀበል ወይም ግለሰቡን ካለው ዜግነት ማላቀቅ የሀገሮች የውስጥ ህግ ጉዳይ መሆኑ ተቀባይነት ያለው አሠራር ነው። በሰፊው የሚሠራባቸውና ሀገሮች ለግለሰቦች የዜግነት መብት ለመስጠት የሚጠቀሙባቸው መርሆች "ዩስ ሳንጉዊንስ" እና "ዩስ ሳሊ" ናቸው። "ዩስ ሳንጉዊንስ" በግለሰቡ ወላጆች ዜግነት ላይ የተመሠረተ ሲሆን "ዩስ ሳሊ" ደግሞ በግለሰቡ የትውልድ ቦታ ላይ የተመሠረተ መርህ ነው። ጋብቻ በሴቶች ዜግነት ላይ የሚያስከትለው ውጤት ደግሞ ሀገሮች በዜግነት ሕጎቻቸው ውስጥ በሰፊው የሚጠቀሙበት ሌላው መርህ ነው።

የአንድን ግለሰብ ዜግነት አስመልክቶ በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ሀገሮች መካከል ክርክር በተነሣ ጊዜ በኖተቦህም ጉዳይ የተጠቀሰውና ከግለሰቡ ጋር ቀጥተኛና ግልፅ ግንኙነት ያለው ሀገር ዜጋ ነው የሚለው መርህ ተግባራዊ ይሆናል። ግለሰቡ በርግጥም ከዚያ ሀገር ጋር ቀጥተኛና ግልፅ ግንኙነት ያለው መሆን አለመሆኑ በርካታና የተለያዩ ጠቀሜታ ያላቸው ሁኔታዎችን በመመልከት ይወሰናል። /እነዚህም ሁኔታዎች የግለሰቡን የዘወትር መኖሪያ፣ የጥቅም ምንጮች፣ የቤተሰብ ትስስር፣ በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ ያለው ተሳትፎ፣ ከአንድ ሀገር ጋር ያለው ትስስር ወይም ትርበት እንዲሁም ይኸው ትስስር በልጆቹ ሥነ ልቡና ላይ ያለውን ተፅዕኖ ... ያካትታል/። በአለም አቀፍ ፍርድ ቤት የኖተቦህም ጉዳይ ላይ የተጠቀሰው የቀጥተኛና ግልፅ ግንኙነት /ጄኑዊን ሊንክ/ ንድፈ ሀሣብ ምንም እንኳ በአንዳንዶች ዘንድ ተቃውሞ ቢገጥመውም አለም አቀፍ ህግ ወደመሆን ደረጃ ያደገ ይመስላል።

- ረ -

ጋብቻ የፈፀሙ ሴቶችን ዜግነት በተመለከተ በ1930 የወጣው የኢትዮጵያ የዜግነት ህግ በወቅቱ ማለትም ከአንደኛው የአለም ጦርነት በኋላ ባሉት ጊዜያት ዜግነትን በተመለከተ በሰፊው ይሠራባቸው ከነበሩት መርሆች የሚለይ አይደለም። በርግጥ የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ ጋብቻ የፈፀሙ ሴቶችን ዜግነት በተመለከተ የሕጉ ድንጋጌዎች በ1930 አካባቢ ከኢትዮጵያ ጋር ዲፕሎማቲካዊና ልዩ ልዩ ግንኙነቶች

በንበራቸው በአብዛኞቹ ሀገሮች ዘንድ በሚሠራበትና በቤተሰባዊ ትምረት /አንድነት/ መርህ ላይ የተመሠረቱ መሆናቸውን ይገነዘባል።

ከ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ በፊት ብዙ ኢትዮጵያውያን በውጭ ሀገር ያለመኖራቸውና ብዙ የውጭ ዜጎችም በኢትዮጵያ ያለመኖራቸው ጉዳይ ከግምት ውስጥ መግባት አለበት። በዚህም ሳቢያ የግለሰቦችን ዜግነት አስመልክቶ ከዚህ ቀደም በተጨባጭ የተነሳ ችግር ካለመኖሩም ባሻገር መልክ የያዙ ሀገራዊ ዜግነት ፅንሰ ሀሳቦችም ሊዳብሩ አልቻሉም። የ1930ው የዜግነት ህግ ከዜግነት ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመፍታት የወጣ የመጀመሪያው ህግ ነው።

በክፍለ ዘመኑ መባቻ ላይ በርካታ የውጭ ኃይሎች በኢትዮጵያ ወኪሎች ነበሩዋቸው። ከእነዚሁ ኃይሎች አብዛኞዎቹ እንዱን ወይም ሌላውን የሀገሪቱን ክፍል በቅኝ ግዛት የመያዝ ምኞት እንደነበራቸው መገንዘብ ይቻላል። ባጠቃላይ በዚያን ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ በሌጋሲዮኖች የተወከሉ ሰባት የሚሆኑ ሀገሮች ሲኖሩ /አሜሪካ፣ ብሪታኒያ፣ ቤልጅየም፣ ፈረንሳይ፣ ግሪክ ጀርመን/ እንዲሁም በቆንስላዎች የተወከሉ ሁለት ሀገሮች፣ ስዊድንና ቱርክ ነበሩ።[79]

በ1908 ፈረንሳይ ክሎቡኮውስኪ በተባለው ወኪልዋ በኩል የክሎቡኮውስኪ ውል በመባል የሚታወቀውን ስምምነት ከአጼ ምኒሊክ ጋር ተፈራረመች። ይህ ውል ሌሎች ጉዳዮችን ጨምሮ በፈረንሣይ ዜጎች መካከል እንዲሁም በፈረንሳይና በኢትዮጵያ ዜጎች መካከል የሚነሱ ክርክሮችን የሚሰማ ልዩ ፍርድ ቤት ለማቋቋም የተደረገ ስምምነት ነው።[80] በጊዜው የነበሩት ብዙዎቹ የውጭ ኃይሎችም በተናጠል ከኢትዮጵያ ጋር ... የወዳጅነት ስምምነት ተፈራርመው ስለነበር የክሎቡኮውስኪ ውል ድንጋጌዎች ለሌሎችም ሀገሮች በሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል።

የፍርድ ቤቱን አወቃቀር በተመለከተ ምንም እንኳ ፈረንሳይ በቆንስላ የሚመሩ ፍርድ ቤቶች እንዲኖሩ አጥብቃ ብትሻም አጼ ምኒሊክ ይህንን ሀሳብ ፈፅሞ አልተቀበሉትም።[81] በዚህም የተነሣ ዜጎቻቸው በክርክሩ ተሳታፊ የሆኑ ሀገሮች

ወኪሎች በአባልነት የሚገኙበትና ኢትዮጵያውያን ዳኞችን የያዘ አንድ ልዩ ፍርድ ቤት ተቋቋመ።

ከካፒቱላሲዮን ውል ድንጋጌዎች አንዱ የልዩ ፍርድ ቤቱ አባል የሆነ ኢትዮጵያዊ የብሪታኒያን፣ የፈረንሳይንና የኢጣሊያን ሕጎች የማወቅ ግዴታ አለበት የሚል ነው።[82] ከዚሁ ጋር በማያያዝ በ1930 ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ተብለው የነገሡትና በዚያው ዓመት የኢትዮጵያን የዜግነት ህግ ያወጡት ራስ ተፈሪ መኮንን በልዩ ፍርድ ቤቱ እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ አባል በመሆን ማገልገላቸውን መጠቆም አስፈላጊ ነው።[83]

የካፒቱላሲዮን ውል በኢትዮጵያ ውስጥ ለዘመናዊ የሕግ ፅንሰ ሀሳቦች እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክቷል። ልዩ ፍትድ ቤቱም በውጭ ዜጎች መካከል የውጭውን ሕግ፣ እንዲሁም በኢትዮጵያውያን ተከራካሪዎች መካከል የኢትዮጵያን ሕግ በመጠቀም ይሠራ ነበር።[84] ስለዚህም በልዩ ፍርድ ቤቱ ፊት ኢትዮጵያዊ የሕግ ፅንሰ ሀሣቦች ከዘመናዊው የአውሮፓ የሕግ አስተሳሰብ ጋር መጋጨታቸው አልቀረም። ከዚሁ ጋር በተያየዘ መልኩ ፍርድ ቤቱ አውሮፓዊ የሕግ ፅንሰ ሀሣቦች ወደ ኢትዮጵያ ሥርዓተ ሕግ ውስጥ እንዲገቡ በቀዳሚ መድረክነት አገልግሏል።

ከኢትዮጵያ የዜግነት ሕግ አንፃር ሲታይ የካፒቱሎውሲ ውል ጠቃሚ አስተዋጽኦ የልዩ ፍርድ ቤቱን የዳኝነት ሥልጣን ለመከለል የኢትዮጵያውያን ዜጎችን ማንነት የመወሰን አስፈላጊነት ማሳየቱ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ልዩ ፍርድ ቤቱ የወደፊቶቹ ኢትዮጵያዊያን ሕግ አውጭዎች በወቅቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ተወክለው ከነበሩ ሀገሮች በተለይም ከብሪታኒያ ከፈረንሳይና ከኢጣሊያ የዜግነት ሕግ ፅንሰ ሀሳቦችና መርሆች ጋር የሚተዋወቁበትን አመቺ መድረክ ፈጥርዋል።

በ1930 ዓ.ም. ያገቡ ሴቶችን በተመለከተ የዜግነት ሕጎቻቸው ለቤተሰባዊ አንድነት ቅድሚያ በሚሰጥ መርህ ላይ የተመሠረቱ እንዲሁም የዜግነት ሕጎቻቸው በጾታዎች እኩልነት መርህ ላይ የተመሠረቱ ሀገሮች ኢትዮጵያ ውስጥ ተወክለው

ነበር። ከነዚህም ውስጥ የአሜሪካና የፈረንሳይ የዜግነት ሕጎች በጾታዎች እኩልነት መርህ ላይ የተመሠረቱ ሲሆን የሌሎች ሕጎች ደግሞ በቤተሰብ አንድነት መርህ ላይ የተመሠረቱ ነበሩ።

በእኀበት 10/1927ቱ የፈረንሳይ ሕግ መሠረት "አንዲት የውጭ አገር ዜጋ የሆነች ሴት አንድ ፈረንሳዊ ሰው ስታገባ የፈረንሳይ ዜጋ የምትሆነው ራሷ በይፋ በምታመለክትበት ጊዜ ወይም በአገርዋ ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት የግድ የባሏን ዜግነት እንድትይዝ የምትደረግ ሲሆን ብቻ ነው። ..." እንዲሁም

"የባዕድ ዜጋ የሆነ ሰው የምታገባ አንድ ፈረንሣዊት በባሏ አገር ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት የባሏን ዜግነት እንድትይዝ በግልጽ ካላስታወቀች በስተቀር የፈረንሣይ ዜግነቷን ይዛ ትቆያለች።"

የሴፕቴምበር 22/1922ቱ ፣የዩናይትድ ስቴትስ ሕግ ከፈረንሣይ ሕግ ጋር በጣም ይመሳሰላል፣

"ይህ ሕግ ከወጣ በኋላ የዩናይትድ ስቴትስ ዜጋ የሆነን ሰው የምታገባ ማንኛዋም ሴት በዚህ ጋብቻ ምክንያት ብቻ የዩናይትድ ስቴትስ ዜጋ አትሆንም ... ሆኖም ለዜግነት ብቁ ሆና ከተገኘች የዩናይትድ ስቴትስ ዜጋ ልትደረግ ትችላለች

..." እንዲሁም "አንዲት የዩናይትድ ስቴትስ ዜጋ የሆነች ሴት ዜግነቷን ስለመተዋ በጽሁፍ ካልገለጸች በስተቀር ይህ ሕግ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በጋብቻዋ ምክንያት የዩናይትድ ስቴትስ ዜጋ መሆንዋ አይቋረጥም ..."።

የ1922ቱ የዩናይትድ ስቴትስ ሕግና የ1927ቱ የፈረንሳይ ሕግ ያገባች ሴት የራሷን ዜግነት እንድትመርጥ የሚያስችላት መብት ለሚጠብቁ ሕጎች ዓይነተኛ ምሳሌዎች ናቸው።

እዚህ ላይ ሁለቱ መንግሥታት በነዚህ ሕጎች አማካይነት ያገቡ ሴቶችን ዜግነት በሚመለከት ቀድሞ የነበራቸውን አቋም ሙሉ በሙሉ መገልበጣቸው ትኩረትን የሚስብ ነው። የ1855ቱ የዩናይትድ ስቴትስ ሕግ፥ በ1907ቱ ሕግ እንደተጠናከረው፥ እንዲሁም የ1804ቱ የናፖሊዮን ሕግ አንቀጽ 12 እና 19፥ በ1889ኙ ሕግ እንደተሻሻለው፥ ያገቡ ሴቶችን ዜግነት በተመለከተ ከአሁኑ የኢትዮጵያ የዜግነት ሕግ ጋር አንድ ዓይነት ነበሩ። ሕጎቹ ጋብቻ ለሴቷ የባሏን ዜግነት የማሰጠት ውጤት በነበረው የቤተሰብ አንድነት መርህ ላይ የተመሠረቱ ነበሩ። በግልጽ እንደሚታየው የ1930ው የኢትዮጵያ የዜግነት ቅግ ከ1922ቱ የዩናይትድ ስቴትስ ሕግና ከ1922ቱ የፈረንሳይ ሕግ ጋር በቃልም ሆነ በመንፈስ ምንም ዓይነት ተመሳሳይነት የለውም። ለ1930ው ሕግ አውጭ እነኚህ ሕጎች ከሚገባው በላይ ዘመናዊ የሆኑበት ይመስላል።

በሌላ በኩል የኢትዮጵያ የዜግነት ሕግ በዚያን ጊዜ በኢትዮጵያ የተወከሉ የሌሎች አገሮች የዜግነት ሕጎች ውስጥ በሚታዩ ጽንሰ ሃሳቦችና መርሆዎች ላይ የተመሠረተ መሆኑ ግልጽ ነው። ከነኚህ መሐል የቤልጅግ፥ የጣልያን እና የግሪክ[87] የዜግነት ሕጎች ከኢትዮጵያ የዜግነት ሕግ ጋር ጉልህ ተመሳሳይነት አላቸው።

የሜይ 15/1922ቱ የቤልጅግ ሕግ እንዲህ ይላል፥

"አንድ ቤልጅጋዊ ሰው የምታገባ የውጭ አገር ሴት ... የባሏን ዜግነት ትወስዳለች" እንዲሁም

"የሚከተሉት ሰዎች የቤልጅግ ዜግነታቸውን ያጣሉ፥

በባሏ አገር ሥራ ላይ በዋለው ሕግ መሠረት የባሏን ዜግነት የምታገኝ ከሆነ፥ የተወሰነ ዜግነት ያለው አንድ የውጭ አገር ዜጋ የምታገባ ቤልጅጋዊት ሴት።"

ይህ ሕግ ቤልጅጋዊቷ ሴት ዜግነቷን ይዛ መቆየት መፈለጓን በምታስታውቅበት ጊዜ ዜግነቷን ይዛ የመቆየት መብቷን ይጠብቅላታል።

የጃፓን 13/1912ቱ የሚልያን ሕግ እንዲህ ይላል፥

"አንድን ዜጋ የምታገባ የውጭ አገር ዜጋ የሆነች ሴት የሚልያን ዜግነት ታገኛለች ..." እንዲሁም "የውጭ አገር ዜጋ የሆነ ሰው የምታገባ ዜጋ በጋብቻው ምክንያት ለአርሷ የሚተላለፍ ዜግነት ባሏ ያለው ከሆነ የሚልያን ዜግነቷን ታጣለች።"

በመጨረሻ በአክቶበር 29/1856 የወጣው የግሪክ ሕግ ቁጥር 391 እንዲህ ይላል፥ "ግሪካዊ ሰው የምታገባ እንዲት ባዕድ ሴት ግሪካዊት ትሆናለች"። እንዲሁም "የውጭ አገር ዜጋ የሆነ ሰው የምታገባ ግሪካዊት ሴት ጋብቻዋ የባሏን ዜግነት የሚያሰጣት ሲሆን ብቻ የግሪክ ዜግነቷን ታጣለች።" የ1931ዱ የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት በጃፓኑ የሜጂ ሕገ መንግሥት መልክ ስለተቀረጸ[88] የኢትዮጵያው ሕግ አውጭ ለጃፓን የሜጂ ዘመን መንግሥት የሕግ ሥርዓት ልዩ ትኩረት የሰጠ ይመስላል። ምንም እንኳን በ1930 ጃፓን በኢትዮጵያ ውስጥ ለጋሲዮን ወይም ቆንስላ ያልነበራት ቢሆንም የማርች 1899ኙ[89] ሕግ ቁጥር 66 ከኢትዮጵያ የዜግነት ሕግ ጋር ጉልህ ተመሳሳይነት አለው።

የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች እንደሚሉት፥

"አንድ ባዕድ የሆነች ሴት በሚከተሉት ሁኔታዎች የጃፓንን ዜግነት ታገኛለች፥ /1/ የአንድ ጃፓናዊ ሚስት በመሆን"፤ ነገር ግን፥ "እንዲት ጃፓናዊት አንድ ባዕድ የሆነ ሰው በማግባቷ የባሏን ዜግነት ያገኘች እንደሆነ የጃፓን ዜግነቷን ታጣለች።" የ1930ው የኢትዮጵያ የዜግነት ሕግ እንዲህ ይላል፥ አንድ የኢትዮጵያ ዜጋ ከአንድ የውጭ አገር ዜጋ ከሆነች ሴት ጋር የሚያደርገው ሕጋዊ ጋብቻ ለሴትዮዋ ኢትዮጵያን ዜግነት ያሰጣታል። ..." እንዲሁም "አንድ ኢትዮጵያዊት ሴት ከአንድ የውጭ አገር ዜጋ ጋር በውጭ አገር የምትፈጽመው ሕጋዊ ጋብቻ የባሏን ዜግነት የሚያሰጣት ከሆነ ይኸው ጋብቻ የኢትዮጵያ ዜግነቷን ያሳጣታል። ይህ እስካልሆነ ድረስ የኢትዮጵያ ዜግነቷን ይዛ ትቆያለች"።

በ1940ዎቹ እንኳን የ1922ቱ የዩናይትድ ስቴትስና የ1927ቱ የፈረንሳይ ህጎች ያገባች ሴት የራሷን ዜግነት የመምረጥ ነፃነት አላት በሚለው አዲስ ጽንሰ ሃሳብ ላይ የተመሠረቱ በመሆናቸው እንዳልተለመደ እንግዳ ነገር ይቆጠሩ ስለነበር[90] እንደልዩ ሁኔታ ይታዩ እንደነበር እዚህ ላይ ሊገለጽ ይገባዋል።

በ1930 ዓ.ም. በሥራ ላይ የዋለው በኢትዮጵያ ውስጥ በጊዜው ተወክለው የነበሩት የሌሎች ኃይሎች የዜግነት ሕግ ውስጥ ይንፀባረቅ የነበረው መርህ ነበር። በጊዜው በሥፋት ሥራ ላይ ውሎ በነበረው መርህ መሠረት ባገባች ባዕድ ሴት ዜግነት ላይ ጋብቻ የሚያስከትለው ውጤት ያለጥያቄ ተቀባይነት ያገኘ ነበር።[91] ከላይ የተመለከተው የ1930ው የኢትዮጵያ የዜግነት ህግ አንቀጽ 2 የዚህ መርህ ዓይነተኛ ምሳሌ ነው።

- ሰ -

ያገቡ ሴቶችን የዜግነት ህግ አመጣጥና ዕድገት የተመለከተ ከዚህ በላይ የቀረበው አጭር ሐተታ መንግሥታት በዜግነት ህጎቻቸው ውስጥ ሁለት ጽንሰ ሃሳቦችን ሥራ ላይ እንደሚያውሉ አሳይቷል። የመጀመሪያውና ነባሩ ጽንሰ ሃሳብ በቤተሰብ አንድነት መርህ ላይ የተመሠረተ ሲሆን የመርሁ መሠረት ጋብቻ ለሚስት የባሏን ዜግነት የማሰጠት ውጤት አለው። ሁለተኛውና የቅርቡ ጽንሰ ሃሳብ ያገባች ሴት የራሷን ዜግነት የመምረጥ ነፃነት አላት በሚለው መርህ ላይ የተመሠረተ ሲሆን በመርሁ መሠረት ጋብቻ በራሱ በሚስቲቱ ዜግነት ላይ የሚያስከትለው ምንም ውጤት የለም።

የኢትዮጵያ የዜግነት ህግ በግልጽ የተመሠረተው በነባሩ ጽንሰ ሃሳብ ላይ ነው። ይህም በመሆኑ አንድ ባዕድ ሴት ከአንድ የኢትዮጵያ ዜጋ ጋር የምትፈጽመው ጋብቻ ለሚስቲቱ የኢትዮጵያን ዜግነት የማሰጠት ውጤት አለው፤ ማለትም በጋብቻው ምክንያት ብቻ የኢትየጵያ ዜጋ ትሆናለች። በኢትዮጵያ የዜግነት ህግ አንቀጽ 2 መሠረት ባዕድ ለሆነችው ሴት የኢትዮጵያን ዜግነት የሚሰጣት ጋብቻ ነው።

ስለዚህ መረጋገጥ የሚገባው ነገር ባዕድ የሆነችው ሴት ከአንድ የኢትዮጵያ ዜጋ ጋር ሕጋዊ ጋብቻ መፈፀሟ ብቻ ነው። ይህ ከተረጋገጠ ይኸው በቂ ሆኖ የኢትዮጵያ ዜጋ ትሆናለች። የኢትዮጵያ ዜጋ የመሆንን ምርጫ አለመቀበል ባዕድ ለሆነችው ሴት አልተፈቀደላትም። እንዲሁም በሕጋዊው ጋብቻ ሥነ ሥርዓት ምክንያት የኢትዮጵያ ዜጋ መሆንዋን ለማረጋገጥ የሚያስፈልጉትን ሰነዶች የኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች፣ የመከልከል ምርጫ የላቸውም። ባዕድ ለሆነችው ሴትዮ በኢትዮጵያ ዜግነት የሚሰጣት ጋብቻ በመሆኑ የኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች የሚችሉት ባዕድ የነበረችው ሴት የኢትዮጵያ ዜጋ መሆንዋን በይፋ መግለፅ ብቻ ነው። ባለሥልጣኖቹ ሴትዮዋ የኢትዮጵያ ዜጋ እንድትሆን መወሰን አይችሉም። በኢትዮጵያ የዜግነት ህግ የባለሥልጣኖቹ ተግባር ባዕድ የሆነችውን ሴት የኢትዮጵያ ዜጋ ማድረግ ሳይሆን፣ ዜጋ መሆንዋን በይፋ ማረጋገጥ ነው። ባዕድ የሆነችውን ሴት በተመለከተ የባለሥልጣኖቹ ውሳኔ የሚኖረው ውጤት በአገር ተወላጅ የኢትዮጵያ ዜጎች ላይ ካለው ውጤት የተለየ አይደለም።

በኢትዮጵያ የዜግነት ህግ አንድ የኢትዮጵያ ዜጋ የሆነን ሰው ያገባች ባዕድ ሴት የኢትዮጵያን ዜግነት የምታገኘው የኢትዮጵያ ዜጋ ለመሆን የምትፈልግ መሆንዋን በይፋ ስትገልፅ ወይም ስትስማማ ነው ማለት ጋብቻ ብቻውን በሴትየዋ ዜግነት ላይ የሚያስከትለው ምንም ውጤት የለም የሚለውን አዲስ መርህ ሥራ ላይ ማዋል ይሆናል። አሁን የሚቀረው የስቬትላና ማማዶሻና የአሜሪካን ኮሚኒቲ ት/ቤት ጉዳይ በሚመለከት የውራጃው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ከዚህ ሁኔታ ጋር መስማማቱን መመርመር ነው።

በአንዲት ስቬትላና ማማዶሻ /ከዚህ በኋላ "አቤት ባይ"/ በሚባሉ ሴት እና በአሜሪካን ኮሚኒቲ ት/ቤት /ከዚህ በኋላ "መልስ ሰጭ" በሚባለው/ መሐል እዚሁ አዲስ አበባ ውስጥ በዚህ ጽሁፍ በገጽ 1 ላይ በተጠቀሰው የሥራ ክርክር ያገቡ ሴቶች ዜግነት በኢትዮጵያ ህግ የሚል ጭብጥ ተነስቶ ነበር።

አቤት ባይዋ የሶሺየት ሀብረት ዜጋ ሲሆኑ በሶሺየት ሀብረት ህግ መሠረት ከአንድ የኢትዮጵያ ዜጋ ከሆነ ሰው ጋር በ1979 ምስኮ ውስጥ ተጋብተዋል። አዋጅ 64/68 በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚሠሩ የውጭ አገር ዜጎች በሚያዘው መሠረት የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሥራ ፈቃዳቸውን በየጊዜው ማደሱ እንደተጠበቀ ሆኖ አቤት ባይዋ በ1982 እዚሁ አዲስ አበባ ውስጥ በመልስ ሰጭ ተቀጥረው ነበር።

መልስ ሰጪ የሥራ ፈቃዱን ለማሳደስ ፈቃደኛ ባለመሆኑና አቤት ባይዋ ለሥራው በቂ አይደሉም በሚል ምክንያት የቅጥር ውሉን በመሠረዙ አቤት ባይ ለሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አስማሚ አቤቱታቸውን አቀረቡ። በአቤቱታቸው ውስጥ ያቀረቡት አንዱ ክርክር የኢትዮጵያ ዜጋ የሆነን ሰው በማግባታቸው በ1930ው የኢትዮጵያ የዜግነት ህግ መሠረት እራሳቸው የኢትዮጵያ ዜጋ ስለሆኑ የሥራ ፈቃድ እንዲያሳድሱ ስለማያስፈልጋቸውና የሥራ ፈቃዱ አለመታደስ ለቅጥር ውሉ መሠረዝ ምክንያት መሆን አይችልም የሚል ነው።

የአቤት ባይዋን ዜግነት በሚመለከተው ጉዳይ ላይ ከአንድ የኢትዮጵያ ዜጋ ከሆነ ሰው ጋር በፈፀሙት ጋብቻ ምክንያት ብቻ የኢትዮጵያ ዜጋ ሆነዋል ሲል አስማሚው ወሰነ።

ጉዳዩ በይግባኝ ሲቀርብለት የአውራጃው ፍ/ቤት የሠራተኛ ጉዳይ ችሎት የአስማሚውን ውሣኔ ገልብጦታል። ለዚህም ከተሰጡት ምክንያቶች መሐል የሚከተሉት አጠያያቂ ምክንያቶች ይገኙበታል።

ሀ/ በ1930ው የኢትዮጵያ የዜግነት ህግ አንቀጽ 2 መሠረት ከአንድ የኢትዮጵያ ዜጋ ከሆነ ሰው ጋር የተጋባች ባዕድ ሴት የኢትዮጵያ ዜጋ ለመሆን ይህንኑ በይፋ ካላስታወቀችና የመጀመሪያውን ዜግነቷን ካልተወች በስተቀር የኢትዮጵያ ዜግነት አታገኝም።

ለ/ የ1930ው የኢትዮጵያ የዜግነት ህግ ጣምራ ዜግነት ስለሚከለክል አቤት ባይዋ በአንድ ጊዜ የሶሺየት ሀብረትና የኢትዮጵያ ዜጋ መሆን አትችልም። አቤት

ባይዋ ትዳዩ ጠቅላይ ፍ/ቤት ቀርቦ በሰበር እንዲታይላቸው ወይም ውሣኔው እንዲሻርላቸው ለዐቃቤ ህግ ጽ/ቤት ጥያቄ ሲያቀርቡ የአውራጃው ፍ/ቤት ውሣኔ ከ1930ው የኢትዮጵያ የዜግነት ህግ ጋር የሚስማማ ስለሆነ ጉዳዩን ወደ ጠቅላይ ፍ/ቤት ለማቅረብ በቂ ምክንያት የለም በማለት ጽ/ቤቱ ጥያቄውን ሳይቀበለው ቀርቷል።

የ1930ው የኢትዮጵያ የዜግነት ህግ አንቀጽ 2 የሚከተለውን ይደነግጋል፥ "አንድ የኢትዮጵያ ዜጋ የሆነ ሰው ከአንድ የውጭ አገር ዜጋ ከሆነች ሴት ጋር የሚያደርገው ሕጋዊ ጋብቻ ለሴትዮዋ የኢትዮጵያ ዜግነት ይሰጣታል።"[92] /የዚሁ አንቀጽ የአማርኛ ቅጂ ምንም እንኳን ቃል በቃል ሲተረጎም ከእንግሊዝኛው ጋር አንድ ባይሆንም በውጤቱ ከእንግሊዝኛው ጋር አንድ ነው/።

ይህ አንቀጽ የውጭ አገር ዜጋ ለሆነች አንዲት ሴት ዜግነት ለመስጠት ሕጋዊ ጋብቻ በቂ ለሆነባቸው የዜግነት ህጎች ዓይነተኛ ምሳሌ ነው። አንቀጹ "የቤተሰብ አንድነት" በሚለው መርህ ላይ የተመሠረተ ስለሆነ በኢትዮጵያ የዜግነት ህግ መሠረት ጋብቻ በአንድ የውጭ አገር ዜጋ በሆነች ሴት ዜግነት ላይ ውጤት እንዳለው ግልጽ ነው።

ይህ አንቀጽ የውጭ አገር ዜጋ የሆነ ሰው ያገባች አንዲት የኢትዮጵያ ዜጋ የሆነችን ሴት ከሚመለከተው የኢትዮጵያ የዜግነት ህግ አንቀጽ 4 ጋር ይጣጣማል። አንቀጽ 4 የሚከተለውን ይላል፥

"በአንዲት የኢትዮጵያ ዜጋ በሆነች ሴት የውጭ አገር ዜጋ ከሆነ ሰው ጋር በውጭ አገር የሚፈፀም ጋብቻ ለሴትዮዋ የባሏን ዜግነት የሚያሰጣት ከሆነ የኢትዮጵያ ዜግነት እንድታጣ ያደርጋታል። ይህ ካልሆነ ግን የኢትዮጵያ ዜግነቷን ይዛ ትቆያለች።

እዚህም ላይ ለቤተሰብ አንድነት መርህ በድጋሚ ትድሚያ የተሰጠ ሲሆን የሴትዮዋ ስምምነት ግምት ውስጥ ሳይገባ ጋብቻው የኢትዮጵያ ዜጋ የሆነችውን ሴት የኢትዮጵያ ዜግነቷን ያሳጣታል። ይህ የሚሆነው ባሏ ዜግነት ባለው መንግሥት ህግ መሠረት የባሏን ዜግነት የምታገኝ ሲሆን ነው። የኢትዮጵያ ዜጋ የሆነች ሴት የኢትዮጵያን ዜግነት ማጣቷ ወይም ይዛ መቆየቷ የሚከሰተው የሴትዮዋ ስምምነት ግምት ውስጥ ሳይገባ ነው።

በአንቀጽ 2 መሠረት አንዲት የውጭ አገር ዜጋ የሆነች ሴት የኢትዮጵያን ዜግነት የምታገኘው እንዲሁም በአንቀጽ 4 መሠረት አንዲት የኢትዮጵያ ዜጋ የሆነች ሴት የኢትዮጵያን ዜግነት የምታጣው ከጋብቻው አስቀድሞም ሆነ በኋላ ስለሁኔታው በይፋ ከማስታወቋ ወይም ስምምነቷን ከመግለጿ ጋር በተያያዘ ምክንያት አይደለም። ስለዚህ በኢትዮጵያ ህግ ያገቡ ሴቶች የኢትዮጵያን ዜግነት ማግኘትና ማጣት የጋብቻ ቀጥተኛ ውጤት ሆኖ ይቆጠራል።

በዚህም ምክንያት የአውራጃው ፍ/ቤትም ሆነ የዐቃቤ ህግ ጽ/ቤት የአቤት ባይን ዜግነት ለመወሰን የጾታዎችን እኩልነት መርህ ሥራ ላይ ያዋሉት በተሳሳተ መንገድ ነው። ምክንያቱም የ1930ውን የኢትዮጵያ የዜግነት ህግ ያወጣው ህግ አውጭ የደነገገው ስለቤተሰብ አንድነት መርህ በመሆኑ ነው። የጾታዎች እኩልነት ለአገቡ ሴቶች የዜግነት ህግ መርህ ሆኖ ማገልገል የጀመረው በቅርብ ጊዜ ውስጥ ሲሆን መርሁ ራሱ ገና በመዳበር ላይ የሚገኝ ነው። በሌላ በኩል፥ የ1930ው የኢትዮጵያ የዜግነት ህግ ያገቡ ሴቶችን ዜግነት በሚመለከት የሴትየዋ ዜግነት የባልየውን ዜግነት ይከተላል የሚለውን አርጌውን መርህ ያቀፈ በመሆኑ ከአዲሱ መርህ ወደኋላ የቀረ ነው።

አሁን ፀንቶ ባለው ህግ ላይ ተመስርተን ስንናገር የአውራጃው ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ ላይ የሰጠው ውሣኔ በኢትዮጵያ የዜግነት ህግ አንቀጽ 2 ላይ የተመሠረተ አይደለም። ባዕድ ለሆነችው ሴት የራሷን ዜግነት የመምረጥ ነፃነት በሚሰጣት ልምድ የተለየ መርህ ላይ በቆመና ፍጹም አዲስ በሆነ ህግ ላይ የተመሠረተ ነው። ዳኛ በሠራው አዲስ ህግ ላይ የተመሠረተ ነው።

በኮመን ሎው ሥርዓትና በሲቪል ሎው ሥርዓት እንደሚደረገው ሁሉ የኢትዮጵያ ዳኛም ህግ አውጭው ለጉዳዩ አግባብ የሆነውን ህግ ሲያወጣ አስቀድሞ ማየት ከተሳነው ሁኔታዎች ጋር ለማስማማት በአዋጅ የወጣውን ህግ በአተረጓጎም የማብራራትና የማዳበር ሚና እንዳለው ይህ ፅሑፍ ይገነዘባል። ሆኖም ዳኛው የህጉን ዕድገት ሲያበረታታ በዳኝነት ሥራው ክልል ውስጥ መወሰን አለበት።

ዳኛው መከተል ያለበት የመጀመሪያው መርህ ዳኛ ህጉን እንዳገኘው ሥራ ላይ ማዋል አለበት የሚለውን መርህ ነው። ዳኛው የህጉን ትርጉም ማግኘት እንጅ ህጉ መሆን ያለበትን አስቀድሞ መገመት አይገባውም። ከዚህ ጋር በተያያዘ የ1930ው የኢትዮጵያ የዜግነት ህግ አርጌ ፅንስ ሀሳብ ላይ የተመሠረተ ህግ መሆኑን መቀበል አማራጭ የለውም።

ይህም ቢሆን ግን ዳኛው ማድረግ የሚችለው ህጉን እንዳገኘው ሥራ ላይ ማዋል ብቻ ነው። ህጉ እንዲጠብቃቸው የወጣበትን ዓላማዎች በመቃወም ብቻ ዳኛው ህጉን ወደጎን መተው አይችልም። ህጉን በሚተረጉምበት ጊዜም ድንጋጌዎቹ መታየት ያለባቸው ህግ አውጭው በአሰበውና በፈለገው መሠረት መሆን አለበት የሚለውን መርህ በሚገባ መገንዘብ አለበት። እንዲሁም ከራሱ ከህጉ መንፈስ ውጭ የሆነን ነገር የህግ አውጭው ፍላጎትና ሃሳብ ማድረግ እንደማይችል መገንዘብ አለበት። "ህግ አውጭው የአሰበውን ነገር በትክክል መግለጽ አልቻለም የሚያሰኝ በቂ ምክንያት ከሌለ በስተቀር የፍ/ቤቱ ኃላፊነት በህጉ ላይ ምንም ነገር መጨመር ወይም ከህጉ ላይ መቀነስ አይደለም።[95] በዚህ ጉዳይ የ1930ው የኢትዮጵያ ህግ አውጭ አዲሱን ዓይነት ህግ ለመደንገግ ፈልጎ ሳይሳካለት ቀርቷል ለማለት አይቻልም።

የዳኝነት ሥራን ሰበብ በማድረግ ፍ/ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ አዲስ ህግ ይዞ የሚወጣ ከሆነ የእኛን የህግ ሥርዓት በሚመለከት የህጉ ነገር ያበቃለታል። ምክንያቱም ህግ የማውጣት ተግባር ህግ የሚፈልገውን ነገር ለህብረተሰቡ የማመልከት ውጤት ስለአለው ነው።

ህብረተሰቡ የዕለት ተዕለት ተግባሩን የሚያካሂደው የወጣው ህግ ከሚፈልገው ሁኔታ ጋር ራሱን በማስማማት ነው። የፍ/ቤቶን ውሳኔ መገመት የማይቻል ከሆነ ህጉ የሚፈልገውን ነገር መፍጠሩና ለህብረተሰቡ ማመልከቱ ይቀራል። ስለዚህም ከዋና ዋና ዓላማዎቹ አንዱን ማስገኘት ይሳነዋል። ፍርድ ቤቱ የሕጉን መሠረታዊ ባህርይና ዓላማ መገንዘብ አለበት፤ ምክንያቱም "በአዋጅ የሚወጣ ህግ የህግ አውጭው ሃሳብና ፍላጎት ውጤት ስለሆነ ነው።[96]

ያገቡ ሴቶችን ዜግነት የሚመለከቱት የ1930ው የኢትዮጵያ የዜግነት ህግ ድንጋጌዎች የጾታዎች እኩልነት ለተረጋገጠበት ለአሁኑ ዘመን ኋላ ቀር በሆኑ ጽንሰ ሃሳቦች ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ቢቻል ያገቡ ሴቶችን ዜግነት በሚመለከት በ1957 ዓ.ም. የተባበሩት መንግሥታት ካወጣው ስምምነት ጋር በሚያጣጥማቸው ሁኔታ እንደገና መጠናት ያስፈልጋቸዋል። ፀሐፊው በህጉ ላይ የሚደረጉ ለውጦች በዳኝነት ውሳኔ ሳይሆን በመደበኛው የህግ አወጣጥ ሂደት ቢደረጉ የኢትዮጵያን የህግ ሥርዓት ይጠቅማል ብሎ ያምናል።

## ማስታወሻዎች

1. ከሣሽ ስዜትላና ማግዳሽ፤ ተከሣሽ የአሜሪካን ኮሚዩኒቲ ት/ቤት፥ አዲስ አበባ አውራጃ ፍርድ ቤት፥ የሥራ ክርክር ችሎት፥ የፍትሐብሄር መዝገብ ቁጥር 1272/77፤ በተጨማሪ ሕጋዊነት፥ ቮልዩም 1፥/የኢትዮጵያ ዐቃቤ ህግ ጽ/ቤት፥ ሚያዝያ 1989/ ገጽ 63ና የሚከተሉትን ይመልከቱ።

2. ክሊቭ ፓሪ፥ "ፕሉረል ናሽናሊቲ ኤንድ ሲትዝንሽፕ ዊዝ ስፔሻል ሪፈረንስ ቱ ዘኮመን ዌልዝ"፥ ብርቲሽ ይር ቡክ ኦቭ ኢንተርናሽናል ሎው፥ ቮልዩም 30/1953፥ ገጽ 244።

3. ሻን ፓንሁይስ፥ ዘ ሮል ኦቭ ናሽናል ኢን ኢንተርናሽናል ሎው /ሌይደን፥ ኤ·ዳብሊው ሲትሆፍ፥ 1959/ ገጽ 150።

4. ክሊቭ ፓሪ፥ ከላይ በተጠቀሰው አርእስት፥ ገጽ 249።

5. ከታች በማስታወሻ ቁጥር 59ና 60 የተጠቀሱትን ይመልከቱ።

6. ለዚህ ነጥብ ጠለቅ ያለ ውይይት፥ ቢ.ሩ ቢክኔል፥ ዘ ናሽናል ኦቭ ሚሪድ ውሜን"፥ ትራንዛክሽንስ ኦቭ ዘ ግሮቲዮስ ሶሳይቲ፥ ቮልዩም 20 ገጽ 118 - 211 ይመልከቱ።

7. ለምሳሌ፥ ከ ናሽናል ኦቭ ሚሪድ ወሜን /ሪፖርት ኦቭ ዘ ሴክሬታሪ ጄኔራል/- ዩናይትድ ኔሽንስ፥ ኒውዮርክ፥ 1963 ጋር ተያይዞ ያለውን ዘ ሰርቬይ ኦቭ ናሽናል ሎውዝ፤ በተጨማሪም ከታች በማስታወሻ ቁጥር 32 በተጠቀሰው ሥራ ውስጥ የተጠቃለሉትን የዜግነት ህጎች ይመልከቱ።

8. አር ኤስ ፍሬዘር፥ "ኤክስፓትሪሼን አዝ ፕራክቲስድ ኢን ግሬት ብርቴይን" ትራንዛክሽንዝ ኦቭ ዘ ግሮትዩስ ሶሳይቲ፥ ቮልዩም 16፥ ገጽ 78 ።

9. በዚያው ጽሁፍ፥ ገጽ 74 ።

10. ጂ ሻን ግልሐን፥ ሎው አመንግ ኔሽንስ አን ኢንተሮዳክሽን ቱ ፓብሊክ ኢንተርናሽናል ሎው /ዘ ማክሚላን ኮምፓኒ፥ 1972/ ገጽ 104 ኮርፐስ ጁሪስ ሰከንደም፥ ገፅ 1138።

11. ኮርንፐስ ጁሪስ ሰከንደም፥ ገፅ 1138።

12. ኤፍ ሊውሊን፥ "ዘ ናሽናሊቲ ኦቭ ማሪድ ውሜን"፥ ትራንዛክሽንዝ ኦቭ ዘ ግሮቲዩስ ሶሳይቲ፥ ቮልዩም 15፥ ገጽ 122።

13. እዚያው ቦታ።

14. በዚያው ጽሁፍ ገጽ 123።

15. እዚያው ቦታ።

16. በዚሁ ጽሁፍ፥ ገጽ 122።

17. እዚያው ቦታ።

18. ኮርፐስ ጁሪስ ሰኩንዱም፥ ገጽ 1139፥ በተጨማሪም ፋሲል ናሆም፥ "/ኢትዮጵያን/ ናሽናሊቲ ሎው ኤንድ ፕራክቲስ"፥ ገፅ 1 /ያልታተመ/፥ ህግ ቤተ መፃህፍት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ። ህጋዊነት፥ ገፅ 64፥ 68ን ይመልከቱ።

19. ኮርፐስ ጁሪስ ሰኩንዱም፥ ገጽ 1138።

20. ሃርቫርድ ሎው ሪቪው፥ ቮልዩም 50፥ ገጽ 831።

21. ኮርፐስ ጁሪስ ሰኩንዱም ገጽ 1138።

22. "ዴቨሎፕመንት ኢን ዘ ሎው፡ ኢሚግሬሽን ኤንድ ናሽናሊቲ"፥ ሃርቫርድ ሎው ሪቪው፥ ቮልዩም 34፥ገጽ 867።

23. ሃርቫርድ ሎው ርቪው፥ ቮልዩም 63፥ ገጽ 886።

24. ፖል ዌስ፥ ናሽናሊቲ ኤንድ ስቴትለስነስ፥ የ2ኛ እትም /1979/ ፖሲም፤ ቶሲል ናሆም፥ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ ውስጥ፥ ቻርት።

25. ኮርፐስ ጁሪስ ሰከንዱም፥ ገጽ 1138፤ ፖል ዌስ፥ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ ውስጥ ገጽ 3ና የሚከተሉትን ይመልከቱ።

26. ለምሳሌ፥ ሃርቫርድ ሎው ርቪው፥ ቮልዩም 50፥ ገጽ 83 ይመልከቱ።

27. ኤፍ ሊውሊን፥ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ ውስጥ፥ ገጽ 106ና የሚከተሉትን ይመልከቱ።

28. ሌውሊን፥ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ ውስጥ፥ ገጽ 134 ውስጥ እንደተጠቀሰው።

29. ክሊቭ ፓሪ፥ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ ውስጧ፥ ገጽ 254።

30. ቢክኔል፥ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ ውስጥ፥ ገጽ 12፤ በተጨማሪም ቪ. ጁ. ቭሶቭ፥ ሲትዝንሽፕ ኦቭ ዘ ዩ ኤስ ኤስ አር፥ ፕሮግረስ ፐብሊሸርስ፥ ሞስኮ፥ 1979፥ ገጽ 82።

31. ዘ ኮሌክሽን ኦቭ ናሽናሊቲ ሎወዝ ኦቭ ቫሪየስ ካንትሪስ አዝ ኮንቴይንድ ኢን ኮንስቲቲዩሽንስ፥ ስታቲዩትስ ኤንድ ትሪቲስ። /ሪቻርድ ፋብሊው ፍሎርኖይ፥ ጁ አር ና ማንሌይ ኦ ሐድሰን/፥ ኒውዮርክ፥ 1929፥ ገጽ 608።

32. ቢክኔል፥ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ ውስጥ፥ ገጽ 112፤ ሌውሊን ከላይ በተጠቀሰው ሥራ ውስጥ፥ ገጽ 121ና በሚከተሉት።

33. ሌውሊን፥ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ ውስጥ፥ ገጽ 125።

34. በዚያው ጽሁፍ፥ ገጽ 127።

35. ሌግ ኦቭ ኔሽንስ ትሪቲ ሲሪስ፥ ቮልዩም 179፥ ገጽ 89።

36. ኮንቬንሽን ኦን ዘ ናሽናሊቲ ኦቭ ማሪድ ውሜን፥ ሂስቶሪካል ባክግራውንድ ኤንድ ኮመንታሪ፥ ዩናይትድ ኔሽንስ፥ ኒውዮርክ፥ 1962፥ ገጽ 9።

37. ይኸው ጽሁፍ፥ ገጽ 11።

38. ይኸው ጽሁፍ ገጽ 7፥ በተጨማሪም ቢከኔል፥ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ ውስጥ፥ ገጽ 113 ።

39. ኮንቬንሽን ኦን ዘ ናሽናሊቲ ኦፍ ማሪድ ውሜን ...፥ ገጽ 11።

40. ይኸው ጽሁፍ፥ ገጽ 12።

41. ቤዚክ ዶኪዩመንትስ ኢን ኢንተርናሽናል ሎው /ሕትመት ኢያን ብሮውሊን፥ 3ኛ ሕትመት/ ክላሬዶን ፕሬስ፥ ኦክስፎርድ፥ 1984 ገጽ 2 ና በሚከተሉት።

42. ይኸው ጽሁፍ፥ 251ና በሚከተሉት።

43. ኮንቬንሽን ኦን ዘ ናሽናሊቲ ኦቭ ማሪድ ውሜን ...፥ ገጽ 17።

44. የዩናይትድ ኔሽንስ ትሪቲ ሲሪስ፣ ቮልዩም 309፣ /1958/ ገጽ 68ና የሚከተሉት።

45. ሺ ሼብሶብ፣ ከላይ በተጠቀሰው አርእስት፣ ገጽ 105።

46. ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 8 ውስጥ የተጠቀሰውን ይመልከቱ።

47. ኮንቬንሽን ኦን ዘ ናሽናስቲ ኦቭ ሜሪድ ውሜን ...፣ አኔክስ።

48. እዚያው።

49. እዚያው፣ በተጨማሪም ቢክኔል፣ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ፣ ገጽ 112-3።

50. ፍሬዘር፣ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ፣ ገጽ 85 ውስጥ እንደተጠቀሰው።

51. ቢክኒል፣ ከላይ በተጠቀሰው ሥሪ፣ ገጽ 114፤ ሊውሌን ከላይ በተጠቀሰው ሥራ፣ ገጽ 115፤ ክሌክሽን ኦቭ ናሽናልቲ ሎውዝ ፣ ገጽ 306።

52. ፍሬዘር፣ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ፣ ገጽ 85፤ ጆሴፍ ኤል ከንፍ፣ "ዘ ኖትቦም ጃጅመንት፣" አሜሪካን ጆርናል ኦቭ ኢንተርናሽናል ሎው፣ ቮልዩም 54 /1960/፣ ገጽ 543፣ 553።

53. "ሎው ኦቭ ዘ ዩኒየን ኦቭ ሶቫሊስት ሪፐብሊክስ ኦን ሲትዚንሽፕ ኦቭ ዘ ዩ ኤስ ኤስ አር፣ ዲሴምበር 1፣ 1978"፣ ሌጅስሌቲቭ አክትስ ኦቭ ዘ ዩ ኤስ ኤስ አር፣ 1977-1979፣ ፕሮግረስ ፐብሊሸርስ፣ ሞስኮ፣ ገጽ 353ና በሚከተሉት።

54. በዚህ ነጥብ ላይ የአለም የሕግ አዋቂዎች የተለያየ አመለካከት አላቸው። ለዚህ ጽሁፍ የሚያገለግለን ግን ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 42 ውስጥ በተጠቀሰው

ቢዚክ ዶክመንት ውስጥ በስታቲዩት ኦቭ ኢንተርናሽናል ኮርት ኦቭ ጀስቲስ አንቀፅ 34 እንደተሰጠው "ፍርድ ቤት ፊት ክሣሽ ወይም ተከሳሽ ሆነው የሚቀርቡት መንግሥታት ብቻ ሊሆኑ ይችላሉ"፣ በተጨማሪም ዳንኤል ቲ መርፊ፣ "ዘ ሬስቴትመንት /ተርድስ/ ኦቭ ሂዩማን ራይትስ ፕሮቪዥንዝ፣ ናቲንግ ኒው፣ ባትሼሪ ዌልካም "፣ <u>ዘ ኢንተርናሽናል ሎውየር</u>፣ ቮልዩም 24/1990/ና የሚከተሉትን ይመልከቱ።

55. ለምሳሌ፣ ሾብሶቭ፣ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ፣ ገጽ 21 ይመልከቱ።

56. አንዳንድ የሕግ አዋቂዎች መንግሥታት ብሄርቻቸውን በመወከል አለም አቀፋዊ ጥያቄዎችን የማቅረብ ግዴታ እንዳለባቸው ይናገራሉ። ለምሳሌ ዳብሊው አር ቢስሾፕ፣ "ናሽናልቲ ኢን ኢንተርናሽናል ሎው"፣ <u>አሜሪካን ጆርናል ኦቭ ኢንተርናሽናል ሎው</u>፣ ቮልዩም 57 /1943/ ገጽ 323፤ ሾቭሶቭ፣ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ፣ ገጽ 31ና የሚከትሉትን ይመልከቱ።

57. የቱኒስና ማሬኮ ናሽናልቲ አዋጅ ክስ፣ <u>ፐርማነንት ኮርት ኦቭ ኢንተርናሽናል ጀስቲስ ሪፖርትስ</u> ሲሪስ ቢ፣ ቁጥር 4፣ ገጽ 24። ዘ ኖትቦም ኬዝ፣ ኢንተርናሽናል ኮርት ኦቭ ጀስቲስ ሪፖርት፣ ገጽ 1955።

58. <u>ሊግ ኦቭ ኔሽንስ ትሪቲ ሲሪስ</u>፣ ቮልዩም 179፣ ገጽ 29፣ አንቀጽ 1።

59. ቫን ፓንሁይስ፣ ከላይ በተጠቀሰው አርእስት፣ ገጽ 55፣ 150 ፓሲም፤ ከንዝ፣ በተጠቀሰው ጽሁፍ፣ ገጽ 545።

60. ማክማሃን ከዜር፣ "ሳብጀክት ሲቲዝን" ናሽናል ኤንድ ፐርማነንት አለጂያንስ"፣ <u>ዬል ሎው ጆርናል</u>፣ ቮልዩም 56 /1946-7/፣ ገጽ 70።

61. ኤፍ ኤ ማን፣ <u>ሬኩዌደ ኮር</u>፣ ቮልዩም 111/1964/፣ ገጽ 9ና በሚከተሉት፤ ኢያን ብሮውንሊ፣ "ፐብሊክ ኢተንተርናሽናል ሎው"፣ <u>ብሪቲሽ ይርቡክ ኦቭ ኢንተርናሽናል ሎው</u>፣ ቮልዩም 39/1965፣ ገጽ 432/3።

62. አር ኤ ሴድለር፣ ዘ ኮንፍሊክት ኦቭ ሎውዝ ኢን ኢትዮጵያ፣ የሕግ ፋኩልቲ፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ፣ 1965፣ ገጽ 6። በተጨማሪም ሾቭሶቭ፣ ከላይ በተጠቀሰው አርእስት፣ ገጽ 49 ላይ እንደሚለው፣ "አንዱ የመንግሥት ሉአላዊነት መሰረታዊ ክፍል /ዜግነትን በሚመለከት ያለ ነፃነት/ ማንኛውም ሉአላዊ መንግሥት ዜጎቹን የሚመለከቱ ማናቸውንም ነገሮች ከማንኛውም ዓይነት የውጭም ሆነ የውስጥ ባለሥልጣን ነፃ ሆኖ ራሱ ይቆጣጠራል" የሚለውን እውነታ ከሁሉም በላይ ይገልጣል።

63. ዘ ሎው ኦቭ ዘ ዩኒዩን ኦቭ ሶቭየት ሶሻሊስት ሪፐብሊክስ ኦን ሲትዝንሺፕ አንቀጽ 4 ዲሴምበር 1፣ 1978 ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 54 እንደተጠቀሰው፣ በዚህም መሠረት ጋብቻ በተጋቢዎች ዜግነት ላይ ምንም ዓይነት ተፅዕኖ የለውም። በ1930ው የኢትዮጵያ ዜግነት ሕግ መሠረት ግን ጋብቻ ለሚስት የባልየውን ዜግነት ያስገኛል።

64. ዮናይትድ ኔሽንስ ትሬቲ ሲሪስ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 44 እንደተገለፀው።

65. በዚሁ ሥራ።

66. ፍሬዘር፣ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ ገፅ 82።

67. እዚያው።

68. ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 57 የተጠቀሰውን ይመልከቱ።

69. ኢንተርናሽናል ኮርት ኦቭ ጄስቲስ ሪፖርት፣ 1965፣ ገጽ 22-23።

70. ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 60 የተገለፀውን ይመልከቱ።

71. ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 57 የተጠቀሰውን ይመልከቱ።

72. ቢስኮፕ፥ ከላይ በተጠቀሰው አርእስት፥ ገጽ 321።

73. በዚያው ጽሁፍ ገጽ 324።

74. ከንዝ፥ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ ገጽ 563-4።

75. ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 53 የተጠቀሰውን ይመልከቱ።

76. <u>ኮንቬንሽን ኦን ዘ ናሽናሊቲ ኦቭ ሚሪድ ውሜን</u> ... እኔክስ።

77. ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 54 የተጠቀሰውን ይመልከቱ።

78. ለምሳሌ ከንዝ፥ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 546፥ ሻን ፓንሁይስ፥ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ በየቦታው፤ ኮስሌር፥ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 48።

79. ሄንሪች ሾሌር፥ <u>ዘ ስፔሻል ኮርት ኦቭ ኢትዮጵያ፥ 1920-1935</u>፥ ስቱትጋርት፥ 1985 ገጽ 48።

80. በዚሁ ጽሁፍ፥ ገጽ 45።

81. እዚያው ቦታ።

82. እዚያው ቦታ።

83. እዚያው ቦታ።

84. እዚያው ቦታ።

85. ኮሌክሽን ኦቭ ናሽናል ሎውዝ ... ገጽ 245።

86. በዚሁ ጽሁፍ፣ ገጽ 608።

87. በዚሁ ጽሁፍ፣ ገጽ 29፣ 363፣ 316።

88. ጀምስ ሲ ኤን ፓል እና ክርስቶፈር ክላፋም፣ ኢትዮጵያን ኮንስቲቲዩሽናል ዲቨሎፕመንት፤ ኤ ሶርስ ቡክ፣ የሕግ ፋኩልቲ፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ፣ 1ኛ ቮልዩም ገጽ 336።

89. ኮሌክሽንስ ኦቭ ናሽናል ሎውዝ ...፣ ገጽ 382።

90. ሻን ፓንሁይስ፣ ከላይ በተጠቀሰው አርእስት፣ ገጽ 161።

91. ለምሳሌ፣ ሌውሊን፣ ከላይ በተጠቀሰው አርእስት፣ ገጽ 133፤ ቢክኔል፣ ከላይ በተጠቀሰው አርእስት፣ ገጽ113፣ ኮንቬንሽን ኦን ዘ ናሽናሰቲ ኦቭ ሜሪድ ውሜን፤ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 32 የተጠቀሰው፤ ኮሌክሽን ኦቭ ናሽናል ሎውዝ ፣ ፓሲም ይመልከቱ።

92. የተጠቃለሉ የኢትዮጵያ ሕጎች፣ 6ኛ ቮልዩም፣ በተጨማሪም ባላምባራስ ማሀተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፣ ዝክረ ነገር፣ 1939፣ ገጽ 183ና የሚከተሉትን /በአማርኛ የተፃፈ/ ውስጥ ይመልከቱ፤ ኤን ግሬይን፣ ዘ ኢትዮጵያን ኢምፓየር ፌዴሬሽን አንድ ሎውዝ፣ ሆተርዳም፣ 1954፣ ገጽ 61ና በሚከተሉት/በእንግሊዝኛ የተፃፈ/ የ1930ው የኢትዮጵጵያ የዜግነት ሕግ ከጣሊያን ወረራ በፊትና የ1931ዱ የኢትዮጵያ የመጀመሪያው ሕገ መንግሥት ተፅፎ ከመውጣቱ ከአንድ ዓመት በፊት ከወጡት ግጎች አንዱ ነው።

93. ሲ ኬ አላን፥ ሎው ኢን ዘ ሜኪንግ፥ ኦክስፎርድ፥ /7ኛ ሕትመት/፥ 1964፥ ገጽ 491።

94. ኤም ፋራኒ፥ ዘ ኢንተርፕርቴሽን ኦቭ ስታቲዩትስ፥ ላሆር ሎው ታይምስ ፓብሊኬሽንስ፥ 1970፥ ገጽ 33።

95. በዚሁ ጽሁፍ ገጽ 107።

96. አለን፥ ከላይ በተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 427።